በአሪዞና አንድነት መረዳጃ ዕድር

ARIZONA ANDNET MEREDAJA EDER

P.O.BOX 24366, Phoenix, AZ 85034

# *BYLAWS*

# *መተዳደሪያ ደንብ*

*ጥር 2018*

*ለሁለተኛ ጊዜ ተሻሽሎ የቀረብ*

*2nd EDITION*

# ማውጫ


ገጽ

ማውጫ ... ... ... ... ... ... 1
መግቢያ ... ... ... ... 3
አንቀጽ 1 ስያሜና የህግ ተገዥነቱ ... ... 4
አንቀጽ 2 ትርጉም ... ... ... 4
አንቀጽ 3 እድሩ የተቋቋመበት ዓላማ ... 5
አንቀጽ 4 አባልነት ... ... ... 6
አንቀጽ 5 የእድሩ አባል መብት ... ... 6
አንቀጽ 6 የአባልነት ግዴታ ... ... 8
አንቀጽ 7 ከእድሩ አባልነት ስለመገለል ... 9
አንቀጽ 8 የእድሩ የገቢ ምንጭ ... ... 10
አንቀጽ 9 የእድሩ ገቢ የሚሰበሰብበት ስልት... 10
አንቀጽ 10 የገንዘብ አሰባሰብ የጊዜ ገደብና ቅጣት 11
አንቀጽ 11 የድሩ አባላት ቤተሰብ መብትና ግዴታ 11
አንቀጽ 12 የእድር አባል በሞት ሲለይ ለአባላት ስለማሳወቅ... ... ... ... 12
አንቀጽ 13 ቅሬታና አለመግባባት የሚፈታብት ዘዴ 13
አንቀጽ 14 የእድሩ መዋቅር ... ... 13
አንቀጽ 15 የጠቅላላ ጉባዔ ሃላፊነት እና ተግባር 13
አንቀጽ 16 የእድሩ አቃቤ ደንብ ሃላፊነትና ተግባር 14
አንቀጽ 17 የእድሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ... 15
አንቀጽ 18 የእድሩ ሰብሳቢ ሃላፊነትና ተግባር ... 15
አንቀጽ 19 ም/ሰብሳቢ ሃላፊነትና ተግባር ... 17
አንቀጽ 20 የእድሩ ዋና ጸሃፊ ሃላፊነትና ተግባር 17
አንቀጽ 21 የም/ጸሃፊ ሃላፊነትና ተግባር ... 18
አንቀጽ 22 የገንዘብ ያዥ ሀላፊነትና ተግባር ... 18
አንቀጽ 23 የሂሳብ ሹም ሃላፊነትና ተግባር ... 19
አንቀጽ 24 የእድሩ ኦዲተር ሀላፍነትና ተግባር 20
አንቀጽ 25 የቡድን መሪዎች ሀላፍነትና ተግባር ... 22

ማውጫ ገጽ

አንቀጽ 26 የአደጋ ወቅት ክፍያ መጠን... ... 22
አንቀጽ 27 ተደራራቢ/ተከታታይ የሞት አደጋ ... 23
አንቀጽ 28 የሞት አደጋ ሲደርስ ለአባላት ስለማሳወቅ....23
አንቀጽ 29 መዋጮ መክፈል ስለማይችሉ አባላት... 23
አንቀጽ 30 መዋጮ በውቅቱ ስለማይከፍል አባል ... 23
አንቀጽ 31 የእድሩ አመራር አባላት በህግ ተጥያቂነትና ከተጠያቂነት ነጻ ስለመሆን ... ... 24
አንቀጽ32 የእድሩ አመራር የአግልግሎት ዘመን .. 25
አንቀጽ 33 የጠቅላላ ጉባኤ የስብሰባ ቀን፤ ቦታ እና ሰዓት 25
አንቀጽ 34 የስብሰባ ስርዓት ... ... ... 26
አንቀጽ 35 በስብሰባ፤ ውሳኔ አሰጣጥ... .... 26
አንቀጽ 36የእድሩ ማህተም አጠቃቀምና አቀማመጥ 27
አንቀጽ 37 የእድሩ አድራሻ ... ... ... .. 27
አንቀጽ 38 የእድሩን ደንብ ስለማሻሻል ... 27
አንቀጽ 39 የእድሩ ድረ ገጽ ... 28
አንቀጽ 40 ደንቡን ያጸደቁ መስራች አባላት ስምና ፊርማ ... ... ... 28

## *መግቢያ*

እንደሚታወቀው የሰውን ልጅ ዘመኑን ሙሉ የማይለየው አብሮት የሚኖር፤ እንደጥላ የሚከተለው፣ በመጨረሻዋም የቁርጥ ቀን የሆነችው፣ አስከፊዋ እና ጎዶሎዋ ቀን ስትደርስ በድንገትም ሆነ ወቅቱን ጠብቆ በሚደርሰው ህልፈተ ሕይወት በሟች ቤተሰብ ላይ ተደራራቢ ጭንቀት እና ችግር ይፈጥራል:: በተለይም ከሃገር ርቆ በስደት ዓለም ለሚኖር፤
ምንም እንኳን የሚወዱትን ቤተሰብ በምንም ጥበብ ከሞት ወደ ህይወት መመለስ ባይቻልም የሟችን አስከሬን በሰላም እና በክብር ማሳረፍ መቻል ግን ትልቅ የህሊና እረፍት ይሰጣል:: ይህም የሚሆነው በቂ የሆነ ቅድመ ዝግጅት ኖሮ አስከሬኑን በወግ ማሳረፍ ከተቻለ ብቻ ነው::አንድ ቤተሰብ የሚወደውን የቤተሰብ አባል ከማጣትም በላይ/ባሻገር/ የቀብሩን ስነ ስርዓት ለማስፈጸም ትልቅ ችግር ከፊት ይደቀናል:: የሞት አደጋ የሚመጣበትን ቀንና ሰዓት አውቆ ተዘጋጅቶ የሚጠብቅ ቢኖር በጣም ኢምንት ነው:: በመሆኑም አብዛኛው አደጋው የሚደርስበት ወገናችን የቀብሩን ስነ ስርዓት በራሱ ማስፈጸም ስለሚሳነው፤ የሟቹን ፎቶግራፍ እና የእርዳታ መሰብሰቢያ ሙዳይ አስቀምጦ መዋጮ እንዲሰበሰብ ማድረግ ግድ ይለዋል:: ይህም በሟች ቤተሰብ ላይ ተጨማሪ ሰቀቀን እና አሸማቃቂ ሁኔታን እንደሚፈጥር ለማንም ግልጽ ነው:

የዚህም ዕድር ብቸኛ ዓላማው በሟች ቤተሰብ ላይ የሚደርሰውን ሸክም ለማቃለል፤ የሟች ቤተሰብም የቀብሩን ሥነስርዓት ለማስፈጸም የሚሆን ገንዘብ ለማግኘት ከመባከን የሚታደግ፤ ጭንቀትን የሚያቃልል፤ ያልታሰበ ዕዳ ውስጥ ከመዘፈቅ የሚያድን፤ የቀብሩንም ስነ ሥርዓት አቀላጥፎ በወቅቱ በክብር የሚያስፈጽም፤ አስከሬኑንም ወደ ሃገር ቤት ለመላክ ከተመረጠ ለቀብር ሥነ ስርዓት የተመደበውን ገንዘብ ከባንክ ወጪ አድርጎ ወደ ሃገር ቤት በመላክ የቀብሩ ስነ ስርዓት በወቅቱ እንዲከናወን የሚያደርግ ፈጥኖ ደራሽ የሆነ መረዳጃ እድር ነው።

ይህ እድር፣ ከዘር ከሃይማኖት፣ ከጾታና፣ ከፖለቲካ ተጽዕኖ ነጻ የሆነ መረዳጃ ማህብር ነው። ***ግቡም የቀብር ስነ ስርዓትን ማስፈጸም ብቻ ነው።*** በመሆኑም በድንበር ያልተከለለ፣ በአኗኗር፣ ተመሳሳይ የቀብር ስነ ስርዓት እና ባህል ያላቸው፤ በማህበራዊ ኑሯቸውም አብሮነት ያላቸው የኢትዮጵያውያን ወዳጆች ሁሉ የሚሳተፉበት እንዲሆን ታስቦ የተቋቋመ መረዳጃ እድር ነው::
ለወገን ደራሽ ወገን በመሆኑ፤ ለራሳችን ደራሾች እኛው እራሳችን በመሆናችን፤ በእያንዳንዳችን እና በቤተሰቦቻችን ላይ ለሚደርስ የሞት አደጋ ያለምንም መጨናነቅና መሸማቀቅ በህብረት /በጋራ/ አደጋውን ለመወጣት ቅድመ ዝግጅት ማድረጉ ብልህነት በመሆኑ ይህንን መረዳጃ እድር አቋቁመናል /መስርተናል/:: ይህም *__ኢትዮጵያዊነትን__* *__የተላበሰ ባህላዊ ኢንሹራንስ ነው::__* ስለዚህ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ፤ ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆነ/የሆነች ሁሉ እንዲሁም ከላይ እንደተጠቀሰው የጎረቤት ሃገር ህዝቦችን ጨምሮ አብሮ ለመደራጀት የሚሹትን ሁሉ የሚያቅፍ መረዳጃ እድር ነው::

ባጠቃላይ የእድሩ አሰራር እንደሚከተለው ነው።

1. አባላትን እየመዘገበ የአንድ ጊዜ የመመዝገቢያ ክፍያ ይሰበስባል።
2. በአንድ አባል ወይም በተመዘገቡ የቤተሰብ አባላት ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ በእድሩ ደንብ መሰረት ለቀብር ስነስርዓት ማስፈጸሚያ የተመደበውን ገንዘብ ከእድሩ የባንክ አካውንት ወጭ አድርጎ በእለቱ ይከፍላል።
3 በአንድ አባል ወይም ቤተሰቡ ላይ የሞት አደጋ ደርሶ ከእድሩ የባንክ አካውንት ወጭ ተደርጎ ከተሰጠ በኋላ እያንዳንዱ አባል እንዲያዋጣ የተመደበውን /ድርሻውን/ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ገቢ ማድረጉን ይከታተላል።
4 አንድ አባል አንድ ጊዜ የአባልነት መመዝገቢያ ከከፈለ በኋል በአባላትና በቤተሰቦቻቸው ላይ የሞት አደጋ ካልደረሰ በቀር እድሩ ምንም አይነት መዋጮ ከአባላት አይሰበስብም::

የእድሩ ዓላማና ተግባሩ ከላይ እንደተገለጸው ሆኖ ዓላማውንና ተግባሩን ሥራ ላይ የሚያውለው በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ይሆናል። ይህ ደንብ በጃንዋሪ 4፣ 2017 ዓ/ም ጀምሮ በእድሩ መስራች ባላት ፊርማ ፀድቆ የአንድነት መረዳጃ እድር መተዳደሪያ ደንብ ሆኗል:

*** *** ***

### *__አንቀጽ 1፡__* *__የእድሩ ስያሜና የህግ ተገዥነቱ__*

1.1 ይህ የመረዳጃ እድር **"በአሪዞና አንድነት መረዳጃ ዕድር"** ተብሎ ይጠራል።
1.2 የተቋቋመውና በድርጅነት የተመዘገበው በሰሜን አሜሪካ ባሪዞና ስቴት አትራፊ ያልሆነ የመረዳጅ ድርጅት ነው።
1.3 እንደመሆኑም በህግ ተገዥነቱና ተጠያቂነቱ አግባብ ባላቸው የአሪዞና ህጎች ይሆናል።

### __አንቀጽ 2፥ ትርጉም__

በዚህ ደንብ ውስጥ የተጠቀሱ ቃላት ወይም ሐረጎች የሚሰጡት ትርጉም፤ የሚያስተላልፉትም መልዕክት የአንድነት መረዳጃ እድር ዓላማና ተልዕኮውን የሚያንፀንባርቅ ብቻ ነው:: ከዚያ ውጭ የሚሰጥ ትርጉም በእድሩ ተቀባይነት አይኖረውም::

2.1 ***<u>የአርማው (የሎጎው) ትርጓሜ</u>፤*** *ኢትዮጵያውያን ፤ ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና ከእነርሱ ጋር በህጋዊ ጋብቻ የተሳሰሩ የሌላ አገር ዜጎች በኢትዮጵያዊነት ድባብ ስር ተጠልለው በባንዲራዋ አሸብርቀው ያቋቋሙት የቀብር ሥነ ስራዓት ማስፈጸሚያ እድር መሆኑን የሚገልጽ እና* ***የአንድነት መረዳጃ እድርን*** *ዓላማና ተልእኮን የሚያንጸባርቅ አርማ ነው። <u>ከአንድነት እና ከኢትዮጵያዊነት</u> ውጪ የተለየ ትርጉም አይኖረውም።*

2.2 ለአባልነት ***<u>መመዝገቢያ ክፍያ፤</u>*** አንድ አባል አስፋላጊውን የመመዝጋቢያ ፎርም ሞልቶ በአባልነት ሲመዘገብ ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚከፈል ክፍያ ነው።

2.3 ***<u>መዋጮ</u>***:-የእድሩ አባላት ለቀብር ሥርዓት ማስፈጸሚያ እንዲውል በነፍስ ወከፍ የሚያዋጡት (የሚከፍሉት) ገንዘብ ነው::

2.4 **<u>ቡድን</u>**:- እያንዳንዱ አባል ለእድሩ ዓላማ የሚውለውን ገንዘብ ድርሻውን በወቅቱ ገቢ ለማድረግ እንዲያስችል ታስቦ አባላትን በቡድን በቡድን መድቦ መዋጮውን የሚሰበስብበት ቀልጣፋ የአሰራር ስልት ነው::

2.5 **<u>ቡድን መሪ</u>**:-በሥሩ የተመደቡትን ሐያ አባላትን የሚያስተባብር፣ የሚቀሰቅስ፣ በስሩ ከተደራጁ አባላት መዋጮ የሚሰበስብ፣ ለአባላቱ አስፈላጊውን መረጃ የሚያስተላልፍ የእድሩን ሥራ የሚያስተባብር የሚያንቀሳቅስ ቁልፍ የሆነ የእድሩ አንድ ዘርፍ ነው::

2.6 **<u>የአባል ተወካይ ወይንም ተጠሪ፤</u> አባሉ በማይኖርበት ወቅት አባሉን ወክሎ ከእድሩ አመራር ጋር የሚሠራ፡**

2.7 **<u>ህጋዊ ተወካይ፤</u> አባሉ በቅጽ ሦስት ላይ ፈቅዶ የወከለው ግለሰብ ሲሆን ከእድር አባላትም ውጪ፤ የእድር አባል ያልሆነም ግለሰብ ተወካይ ሊሆን ይችላል**

2.8 **<u>የመመዝገቢያ ፎርም ቅጽ 3</u> ግለሰቦች ፈቅደው የእድሩ አባል ሆነው ሲመዘገቡ የሚሞሉት ቅጽ ሲሆን ወላጆቻቸውን እና ከ 21 ዓመት በታች የሆኑ ልጆቻቸውን እና ሙሉ አድራሻተውን የሚሞሉበት ፈርም ነው።**

### <u>አንቀጽ 3፦ እድሩ የተቋቋመበት ዓላማ</u>

3.1 በአሪዞና ስቴት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፤ ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና ተመሳሳይ ባህል፤ ወግ እና የቀብር ስርዓት ያላቸው የኢትዮጵያውያን ወዳጆች የሆኑ ግለሰቦች ተሰባስበው የተደራጁበት መረዳጃ እድር በመሆኑ፤ በእድሩ አባላት እና በእድሩ ደንብ ውስጥ በታቀፉ የአባላት ቤተሰብ ላይ የሞት አደጋ በደረሰ ወቅት የቀብሩን ስነስርዓት በሕብረት እና በአንድነት በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማስፈጸም እንዲያስችል ታስቦ እና ታቅዶ የተመሰረተ መረዳጃ እድር ነው።

3.2 አንድ የእድር አባል በቤተሰቡ ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ ባስቸኳይ ለእድሩ አመራር በማሳወቅ በእለቱ ደንቡ የሚፍቅደውን ክፍያ ተቀብሎ የቀብሩን ሥነስርዓት ያስፈጽማል።

3.3 ከዚህ አሰራር ውጪ የሚችን ፎቶግራፍ ለጥፎ መሰበወርቅ አስቀምጦ ወይንም በሌላ ቀጥተኛ መልክ የእርዳታ እጅ እንዲዘረጋለት መጠየቅና፤ ገንዘብ መሰብሰብ በጭራሽ አይቻልም ይህን የሚያደርግ አባል እድሩ የተቋቋመበትን ዋና ዓላማ የተላለፈ፤እና የተጻረረ በመሆኑ ከእድሩ ምንም አይነት የገንዘብ እርዳታ አይደረግለትም። ይኸንን ዓይነት እርዳታ መሰብሰቡ ባለመታውቁ ወይንም በሌላ ስህተት የዕድሩ ክፍያ ተሰጥቶ ከሆነም የተሰጠውን ዕርዳት ተመላሽ ያደርጋል።

### <u>አንቀጽ 4. ፡ አባልነት</u>

የሚከተሉትን የአባልነት ችሎታዎች (qualifications) እና ግዴታዎች የሚያሟላ ግለሰብ የአሪዞና አንድነት መረዳጃ ዕድር አባል ሊሆን ይችላል።

4.1 ማንኛውም ኢትዮጵያዊ፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊ እና ተመሳሳይ የቀብር ሥነስርዓት፤ባህልና ወግ ያላቸው የጎረቤት አገር ሕዝቦች፤ የኢትዮጵያውያን ወዳጆች ከ21 ዓመት በ ላይ የሆኑ ሁሉ፤

4.2 የእድሩን መተዳደሪያ ደንብ ሙሉ ፈቃደኛ ሆኖ የተቀበለ/የተቀበለች፣

4.3 እድሩ የተቋቋመበትን ዋና ዓላማ የተረዳ/የተረዳችና አምኖበት/አምናበት/ ከተቀበለ/ ከተቀበለች፣

4.4 በእድሩ አባላት መመዝገቢያ ቅጽ ሥስትን ሞልቶና ፈርሞ የተመዘገበ/የተመዘገበች እና ምዝገባውም በእድሩ አመራር አባላት ፊርማ ከጸደቀ፤

4.5 የመመዝገቢያና የአባልነት መዋጮ ክፍያን አሟልቶ የከፈለ/የከፈለች።

4.6 ፌብሪዋሪ ***<u>10.2018</u>*** ዓ/ም በተደረገው የጠቅላላ አባላት ጉባኤ ውሳኔ መሰረት፤ ከዚህ ቀን ጀምሮ አንድ አባል የመመዝገቢያ እና የአባልነት ክፍያ ክፍሎ ቅጽ ሦስትን ከሞላበት ቀን ጀምሮ የእድሩ ሙሉ ተጠቃሚ ለመሆን የሦስት ወራት***<u>( የ90 ቀናት)</u>*** የቆይታ ጊዜ ይኖረዋል። በዚህ የዘጠና የቆይታ ቀናት አንድ የእድር አባል ቢሞት መዋጮ አያዋጣም። በራሱም ላይ ሆነ ባስመዘገባቸውቤተሰብ አባላት መሀልም የሞት አደጋ ቢከሰት ከእድሩ ምንም ዓይነትአገልግሎት ወይም የገንዘብ ክፍያ አያገኝም። አገልግሎት ማግኘት የሚችለው የሦስት ወራት የቆይታ ጊዜውን ካጠናቀቀ በኋላ በዘጠና አንደኛው ቀን***<u>(በ91 ኛው ቀን)</u>*** ነው። በንኡስ አንቀጽ 4.1 እስከ ንኡስ አንቀጽ 4.6 የተገለጹትን ነጥቦች የተቀበለ/የተቀብበለች የእድሩ አባል መሆን ይችላል። ትችላለች

### ***<u>አንቀጽ 5፤ የእድሩ አባላት መብት</u>***

5.1 አንድ አባል እራሱና በእድሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በአባላት መመዝገቢያ ቅጽ ውስጥ ካስመዘገባቸው የቤተሰብ አባላት መሃል የሞት አደጋ ቢደርስባቸው በእድሩ በደንቡ የተደነገገው የገንዘብ መጠን ከእድሩ የባንክ አካውንት በዕለቱ ወጪ ተደርጎ የቀብሩ ስነስርዓት እንዲፈጸም ያደርጋል።

5.2 አባሉ ወይም ቤተሰቡ የሚችን አስከሬን ወደ አገር ቤት ለመላክ ከፈለጉ እድሩ ለቀብር ስነስርዓት ማስፈጸሚያ እንዲውል የመደበውን የገንዘብ መጠን ከእድሩ የባንክ አካውንት ወጭ አድርጎ አስከሬኑ ወደ ሃገር ቤት እንዲሸኝ ያመቻቻል።

5.3 በማንኛውም ጊዜ እና ቦታ እድሩን በተመለከተ በሚደረግ ስብሰባ ላይ በመገኘት ያለምንም ገደብና ተጽዕኖ በነጻ ሐሳቡን የማሰማት መብት አለው።

5.4 የእድር አመራር ምርጫ በሚካሄድበት ወቅት በሰዓቱና በቦታው ተገኝቶ የመምረጥና የመመረጥ መብት አለው። ባል እና ሚስት ሁለቱም የእድሩ አባላት ናቸው፤ ይሁን እንጂ ሁለቱም በአንድ የምርጫ ወቅት ለአመራር ቦታ ተመርጠው ሊያገለግሉ አይችሉም። በተናጠል በተለያየ ወቅት ተመርጠው ሊያገለግሉ ይችላሉ።

5.5 ሃያ አንድ (21) ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነው እና ደንቡ የሚፈቅድለት ማንኛውም ሰው በግንባር ቀርቦ በመመዝገብ የእድሩ አባል መሆን ይችላል። በአባቱ ወይንም በእናቱ አባልነት የእድሩ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም።

5.6 *ባልና ሚስት ለአንድ ጊዜ ብቻ የአባልነት እና የመመዝገቢያ ክፍያ ሁለት መቶ ሐምሳ ዶላር ከከፈሉ የእድሩ አባላት ናቸው።*

5.7 *ባልና ሚስት ለአንድ ጊዜ ብቻ የአባልነት እና የመመዝገቢያ ክፍያ ከከፈሉ በአንድ አባል ላይ ወይም በቤተሰቡ ላይ የሞት አደጋ ደርሶ ከእድሩ ባንክ አካውንት ወጪ ተደርጎ ከተከፈለ በኋላ ከባንክ የወጣዉን ገንዘብ መልሶ ገቢ ለማድረግ ለሚደረገው መዋጮ እንደ አንድ አባል ብቻ ይከፍላሉ እንጂ በተናጠል አይከፍሉም።*

5.8 ከኢትዮጵያዊ ወይም ከትውልደ ኢትዮጵያዊ ጋር በሕጋዊ ጋብቻ ተጣምሮ አብሮ የሚኖር/የምትኖር የማንኛውም አገር ዜጋ ሙሉ አባል ሆኖ ለመመዝገብ ይችላል/ትችላለች።

5.9 ማንኛውም ሰው አባል ለመሆን በአሪዞና ስቴት የነዋሪነት መታወቂያ ላይ ባለው ስም፣ መረጃና አድራሻ መሰረት በአካል ተገኝቶ የአባልነት ቅጽ መሙላት አለበት።

5.10 አንድ ሰው የእድሩ አባል ከሆነ በኋላ የመኖሪያ አድራሻ ቢቀይር እና ወደ ሌላ ስቴት ቢሄድ እድሩ ከእሱ የሚፈልገውን ሁሉ ከአገኘ አባሉም ገዴታውን ካሟላ በአባልነት መቀጠል ይችላል። **የአሜሪካን አግር ኑሮውን ትቶ ወደ ኢትዮጵያ ወይም ወደሌሎች አገሮች ጠቅሎ የሄደ አባል ከእድሩ ይሰናበታል።**

5.11 ማንኛውም ሰው የእድሩ አባል የመሆን መብቱ የሚረጋገጠለት የአባልነትና፤ የመመዝገቢያ ክፍያውን ከፍሎ እና የአባልነት ፎርሙን ሞልቶ ሲገኝና በእድሩ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ነው።

5.12 አንድ አባል በእድሩ ውስጥ የተጠቀሰውን መብት እና ጥቅሙን በህይወት እያለ ለሌላ ሰው አስልፎ መስጠት አይችልም። ይሁን እንጂ አባሉ ከሞተ በኋላ የአሪዞና ነዋሪ የሆነ ህጋዊ ወራሹ በእሱ መብት በአባልነት ሊቀጥል ይችላል።

5.13 አንድ አባል እራሱ ወይም ባለቤቱ ከአሜሪካ ውጭ ሆነው የሞት አደጋ ቢደርስባቸው በዚህ ደንብ መሠረት ለቀብር ማስፈጸሚያ የተመደበው ከእድሩ የባንክ አካውንት ወጭ ተደርጎ ለአባሉ/ለአባሏ ወይም በሕጋዊ መንገድ ለተወከለ ተወካይ ይከፈላል።

5.14 እያንዳንዱ አባል በመምረጥም በመመረጥም፤ድምጽ በመስጠትም በእድሩ የመጠቀም መብቱ እኩል ነው።

5.15 አባሉ/አባሏ ከዚህ ዓለም በህልፈተ ህይወት ሲለይ/ስትለይ የቀብሩን ስነ ስራዓት ለማስፈጸም ክፍያ ለመፈጸም እድሩ ከባል ወይም ከሚስት ጋር ተገናኝቶ በመነጋገር የቀብሩን ሥነስራዓት ያስፈጽማል። ይህ ካልሆነ በአባላት መመዝገቢያ ቅጽ ፫ መሰረት ከህጋዊ ተወካዮች ጋር ይሰራል።

## <u>አንቀጽ 6 የአባልነት ግዴታ</u>

6.1 በእድሩ መተዳደሪያ ደንብ የተደነገገውን የአባልነት ክፍያ $ 100.00 የመመዝገቢያ $25.00 በወቅቱ የከፈለ፤

6.2 በአባሉ ወይም በደንቡ የታቀፉ በአባላት መመዝገቢያ ቅጽ የተመዘገቡ የአባላት ቤተሰብ ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ ማዋጣት የሚገባውን ክፍያ በተሰጠው የጊዜ ገደብ አጠቃሎ ገቢ ማድረግ:: ክፍያውን ያለበቂ ምክንያት ያዘገየ አባል በቀጣዩ አስራ አምስት ቀናት ውስጥ ከነቅጣቱ አሟልቶ ማስገባት አለበት። በዚህ በሁለተኛው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከነቅጣቱ ገቢ ካላደረገ በሠላሳ አንድኛው ቀን በቀጥታ ከእድሩ ይሰናበታል:: ይሁን እንጂ ይህ ግለሰብ ተመልሶ አባል ለመሆን በጽሁፍ ከተጠየቀ፤ እንደ አዲስ አባል ተመዝግቦ የአባልነት እና የመመዝገቢያ ክፍያ ክፍሎ አባል መሆን ይችላል::

6.3 በአባሉ ቤተሰብ ውስጥ ለውጥ ከተፈጠረ ማለትም የተመዘገበው ልጅ እድሜ ሀያ አንድ ዓመት መሙላቱን፤ባል እና ሚስት ከተፋቱ፤ የአባላት ወላጆች ገቢ ለውጥ ካሳየ፤ የስልክ እና የአድራሻ ለውጦች ሲያደርግ እና ሌሎችም ተዛማጅ ለውጦች ከተፈጠሩ አባሉ በወቅቱ ለእድሩ ጽሕፈት ቤት ማሳወቅ አለበት።

6.4 ባል እና ሚስቱ ከተፋቱ ፍችው እንደተፈጸመ ውድያውኑ አባሉ ለእደሩ አመራር የፍችውን ህጋዊ ሰነድ በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፤ ባል እና ሚስቱ በእድሩ አባልነት ለመቀጠል ከፈለጉ ሁለቱም በተናጠል የአባልነት እና የመመዝገቢያ ክፍያ ሳይከፍሉ በየግላቸው የመመዝገቢያ ፎርም ቅጽ 3 (ሦስትን) ብቻ ሞልተው በአባልነት መቀጠል ይችላሉ::

6.5 አንድ የእድር አባል በእድሩ ውስጥ በማንኛውም ዘርፍ አገልግሎት እንዲሰጥ በእድሩ አመራር ሲጠየቅ ያለምንም ማቅማማት እና ተቃውሞ ኃላፊነቱን ተቀብሎ ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለበት።

6.6 አባሉ እራሱን እና የእድሩ መመሪያ ህጉ የሚፈቅድላቸውን የቤተሰቡን አባላት በአባላት መመዝገቢያ ቅጽ ሦስት ላይ መሙላት አለበት ይህን

ያላደረገ የእድር አባል በቤተሰቡ ላይ የሞት አደጋ ቢደርስ ምንም አይነት አገልግሎት አያገኝም።

6.7 እያንዳንዱ አባል እድሩ በሚጠራው ዓመታዊ ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ግዴታው ነው። በስብሰባ ላይ የማይገኝ አባል ሓያ አምስት ዶላር፡($25) ይቀጣል። ይህንንም ሀያ አምስት ዶላር ቅጣት በሰላሳ ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት። በሁለተኛ ጊዜም ተመሳሳይ ድርጊት ከፈጸም $25 ዶላር በተጨማሪ ይቀጣል። ለሦሥተኛ ጊዜ በዓመታዊ ስብሰባ ላይ ካልተገኘ ከእድሩ ይሰናበታል። ይሁን እንጂ አንድ አባል ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት በስብሰባ ላይ መገኘት የማይችልበት ሁኔታ ከተፈጠረ፤ ከስብሰባው ቀን ቀደም ብሎ ለአመራሩ ማሳወቅ አለበት። አመራሩም ሁኔታውን አገናዝቦ አሳማኝ ሆኖ ካገኘው ይቀበለዋል። ጥያቄው አሳማኝ ሆኖ ካላገኘው አይቀበለውም። አባሉም ጥያቄው ተቀባይነት ካላገኘ በስብሰባው ሰዓት መገኘት አለበት። ካልተገኘ ቅጣቱ ይፈጸምበታል።

6.8 አንድ የእድር አባል በራሱ ወይም በድሩ መመዝገቢያ ቅጽ ሦስት ላይ ካስመዘግባቸው ከቤተሰቡ አባላት መሐል አንዱ በሞት ቢለይ ለሟች ቀብር ሥነስራዓት ማስፈጸሚያ የሚሆን አሥር ሺህ ዶላር ከእድሩ ባንክ አካውንት ወጪ ተደርጎ ስለሚሰጥ፤ በተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት ታቅዶ የሟችን ፎቶ ለጥፎ ትንሽ ሳጥን አስቀምጦ እርዳታ መሰብሰብ የእድሩን ዋና አላማ የሚጻረር የሚያፈርስ በመሆኑ በፍጹም የተከለከለ እና የተወገዘ ነው። ይህንን እድሩ የተቋቋመበትን አብይ አላማ ተላልፎ የተገኘ የእድሩ አባል ለቀብር ስነሥራዓት ማስፈጸሚያ የተመደበውን አሥር ሺህ ዶላር አይሰጠውም። በስህተት ቢሰጠውም እንኳን ተመላሽ እንዲያደርግ ይገደዳል።

## አንቀጽ 7 ከእድሩ አባልነት ስለመገለል፤

7. 1. የዕድሩን አላማ የሚያኮስስ፤ የሚያደናቅፍ፣ በታኝ እና ከፋፋይ ተግባር ሲፈጽም ከተገኘ፤

7.2 በእድሩ አባላት መሃል የፖለቲካ፣ የሐይማኖት፤ የጎሳ ፤ የጎጥ እና የጾታ ልዩነት የሚያንጸባርቅ፤ አባላትንም የሚከፋፍል ተግባር ሲፈጽም የተገኘ፤

7.3 የእድሩን አላማ እና ተልዕኮ በማጣመም ወደ ሌላ አቅጣጫ ለማስያዝ ፤ የእድሩን መተዳደሪያ ደንብ የሚፈታተን ተግባር ሲፈጽም ወይም ሲያራምድ የተገኘ፤

7.4 በእድሩ አባላት መሃል ቡድናዊ ስሜት እንዲፈጠር ሲገፋፋ ወይም ፣ አባላትን ሲከፋፍል ፤ሲያሴር የተገኘ፤

7.5 ከድሩ የማይገባውን ጥቅም ወይም አገልግሎት ማግኘት ፤ ወይም ለማግኘት አቅዶ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ ከእድሩ አባልነት ይወገዳል።

7.6 ከላይ ከተራ ቁጥር 7.1 እስከ ተራ ቁጥር 7.5 ከተዘረዘሩት መሀል አንዱን ጥፋት እንኳን መፈጸሙ በመረጃ የተረጋገጠበት አባል፡-

7.6.1 ለመጀመሪያ ጊዜ ምክር አዘል የቃል ማስጠንቀቂያ በአመራሩ ይሰጠዋል።

7.6.2 ለሁለተኛ ጊዜ በጥፋት ላይ ተሰማርቶ መገኘቱ በመረጃ ከተረጋገጠበት የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

7.6.3 በሦስተኛ ጊዜ ጥፋተኛነቱ በማስረጃ ከተረጋገጠ በጽሑፍ ይሰናበታል::

7.7 በንዑስ አንቀጽ 7.6 መሠረት ከአባልነት የሚገለል ወይም በፈቃዱ ራሱን ከእድሩ አባልነት የሚያገል ከእድሩ ምንም አይነት ተመላሽ ገንዘብ ወይም ድጎማ አይደረግለትም፤ መጠየቅም አይችልም።በጥፋት ምክንያት ከእድሩ የተሰናበተ አባል ተመልሶ አባል ለመሆን ጥያቄ ቢያቀርብ አይፈቀድለትም።

## አንቀጽ 8: የእድሩ የገቢ ምንጭ

የአንድነት መረዳጃ እድር ዋነኛ የገቢ ምንጭ ከአባላት የሚሰበሰበው መዋጮ ሲሆን የሚቀጥሉትን የገቢ ምንጮች ያጠቃልላል::

8.1 ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚከፈል የአባልነትና የመመዝገቢያ ክፍያ $125.00 ዶላር፤

8.2 የአባላት መዋጮ ማለትም፡ የእድሩ አባል ወይም በእድሩ የአባላት መመዝገቢያ ቅጽ የተመዘገቡ የአባል ልጆችና በአባላት ወላጆች ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ እያንዳንዱ አባል የሚያዋጣው መዋጮ፤

8.3 ከድርጅቶች ወይም ከግለሰቦች የሚገኝ የገንዘብ ወይም የአይነት ስጦታ፤

8.4 እድሩ የተመሰረተበትን ቀን ምክንያት በማድረግ በሚደረግ ዓምታዊ በዓል ዝግጅት እድሩ የተቋቋመበትን አቢይ አላማ ሳይስት የእድሩን ገቢ ለማዳበር በተለያየ መንገድ ከሚደረግ ገቢ ምንጭ የሚገኝ ገቢ እና፤

8.6 እንደአስፈላጊነቱ ለሥራ ማስኪያጃ የሚውል በአባላት መልካም ፈቃድ እና ውሳኔ መሰረት ከአባላት የሚሰበሰብ መዋጮ ነው።

## አንቀጽ 9: የእድሩ መዋጮ ገቢ የሚደረግበት እና የገንዘብ አወጣጥ ስልት ፡

9.1 ለእድሩ የሚደረጉ ክፍያወች በሚከተሉት መንገዶች (ስልት) በመጠቀም ገቢ ማድረግ ይቻላል።

9.1.1 በካሽ፣ (በጥሬ ገንዘብ)፤

9.1.2 በቼክ፤

9.1.3 በመኒ ኦርደር፤

9.1.4 በኦንላይንና፤

9.1.5 በባንክ ዳይሬክት ዲፖዚት ።

9.2 አንድ አባል ክፍያውን ገቢ ያደረገበትን ዘዴ የሚያሳይ ሰነድ ወይንም ተቀባይነት ያለው መረጃ በማቅረብ ከገንዘብ ያዡ ወይንም ከቡድን መሪው የእድሩን ህጋዊ ደረሰኝ መቀበል አለበት።

9.3 በነኡስ አንቀጽ 9.1.1፤ 9.1.2፤ ወይንም 9.1.3 መንገድ ለገንዘብ ያዡ ወይም ለቡድን መሪዎች በግንባር ቀርቦ መክፈል ይቻላል:: ለገንዘብ ያዡም ይሁን ለቡድን መሪዎች በአካል ተገኝቶ ማንኛውንም ክፍያ የሚያደርግ አባል ወዲያውኑ የእድሩን ሕጋዊ ደረሰኝ ዋናውን ኮፒ ይሰጠዋል::

9.4 የእድሩን ገቢ የመሰብሰብ ሕጋዊ ሐላፊነት ያላቸው ገንዘብ ያዡ፣ እና የቡድን መሪዎች ብቻ ናቸው::

9.5 እነዚህም ህጋዊ አካልነት ያላቸው ገንዘብ ተቀባዮች ገንዘብ ሲቀበሉ ወዲያውኑ የእድሩን ሕጋዊ ደረሰኝ መስጠት አለባቸው:: ገንዘብ ከፋይም ሕጋዊ ደረሰኝ ሳይቀበል ገንዘብ መክፈል የለበትም::

9.6 እነዚህም ሕጋዊ አካላት የሚሰበስቡትን ገንዘብ በአምስት ቀናት ውስጥ እድሩ ባንክ አካውንት የማስገባት ሃላፊነት አለባቸው::

9.7 የእድሩ ገንዘብ የሚንቀሳቀሰው ወይም ማንኛውም ክፍያ የሚፈጸመው በቼክ ብቻ ነው:: ከቼክ ውጪ በጥሬ ገንዘብ ምንም ዓይነት ክፍያ አይፈጸምም።

9.8 በእድሩ የባንክ አካውንት ዴቢት ካርድ እና ክሬድት ካርድ ማውጣት በፍጹም አይቻልም።

## አንቀጽ 10: የገንዘብ መዋጮ አሰባሰብ የጊዜ ገደብና ቅጣት

10.1 አንድ አባል ከዚህ ዓለም በሞት ሲላይ ለእድሩ አባላት በእድሩ አሰራር መንገድ ወይም እድሩ በዘረጋው የመገናኛ ዘዴ ለእድሩ አባላት ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ መዋጮው ተጠቃሎ ገቢ መደረግ አለበት።

10.2 አንድ አባል በተሰጠው የ15 ቀናት (15) የጊዜ ገደብ መዋጮውን ገቢ ካላደረገ ሀያ አምስት ዶላር ቅጣት ይከፍላል።

10.3 በተሰጠው የአስራ አምስት ቀናት(15 ) የጊዜ ገደብ ውስጥ አጠቃሎ መክፈል ያልቻለ የእድሩ አባል በሁለተኛው አስራ አምስት ቀናት ውስጥ ከነቅጣቱ ገቢ ማድርግ አልበት። ይህንን ማድረግ የተሳነው አባል (በ31ኛው) በሰላሳ አንደኛው ቀን ከእድሩ አባልነት ይሰናበታል። የከፈላቸውም የአባልነትና የመመዝገቢያ ክፍያ ወይንም ሌሎች ልዩ ልዩ ክፍያዎችና መዋጮዎች አይመለስለትም። ምንም አይነት የመብት ጥያቄ ሊያነሳ አይችልም::ይሁን እንጂ አንድ ቀን ተመልሶ አባል ለመሆን በጽሁፍ ጥያቄ ካቀረበ እንደ አዲስ ተመዝጋቢ አባል የአባልነት እና መመዝገቢያ ክፍሎ አባል መሆን ይችላል።

## አንቀጽ 11: የእድሩ አባላት ቤተሰብ መብትና ግዴታ

11.1 የእድሩ አባላት ቤተሰብ ማለትም ልጆች፣ እና የአባላት ወላጆች ከዚህ በታች የሚከተለው መብት አላቸው፤

11.1.1 እድሜያቸው ከ21 ዓመት በታች የሆነና በእድሩ አባላት መመዝገቢያ ቅጽ ላይ አባሉ ያስመዘገባቸው ልጆች የእድሩ ተጠቃሚዎች ናቸው። እንደመሆኑም ለአባልነትና ለመመዝገቢያ የሚሆን ምንም አይነት ክፍያ ሳይፈጽሙ የእድሩ ተጠቃሚዎች ናቸው። የሞት አደጋ ሲደርስባቸው እድሩ ከባንክ አካውንቱ አሥር ሺህ ዶላር ወጪ አድርጎ የቀብሩን ሥነስራዓት ያስፈጽማል። ለቀብሩ ሥነ ስርዓት ማስፈጸሚያ መዋሉን የእድሩ አመራር ያረጋግጣል። ለልጆች የሞት አደጋ የሚደረገው አርዳታ አስክሬኑ ካስመዘገበው ወላጅ ቤት ሲወጣ ብቻ ነው።

11.1.2 እድሜያቸው ከ21 ዓመት በላይ ሆኖ ህመምተኛ ወይም አካል ጉዳተኛ የሆኑ እና መሥራት የማይችሉ፣ መሥራት አለመቻላቸው በሕክምና የተረጋገጠ የአባል ልጆች የእድር አባል ሆነው ለመዝገብ የሚያስችል ገቢ እስከሌላቸው ድረስ የእድሩ ተጠቃሚዎች ናቸው።

11.1.3 ልጆች የሚመዘገቡት በአንድ ወላጅ ሥር ብቻ ነው። እናት እና አባት ተለያይተው የሚኖሩ ከሆነ እና ሁለቱም በየግላቸው የእድሩ አባላት ከሆኑ፡ ልጁ ወይም ልጆቹ ሊመዘገቡ የሚችሉት በእናታቸው ወይም ባባታቸው ከሁለት ባንዱ ሥር ብቻ ነው።

*11.1.4* የገቢ ምንጭ የሌላቸው ወይም ገቢያቸው እጅግ ዝቅተኛ ሆኖ የልጆቻቸው ጥገኛ የሆኑ የአባል ወላጆች (እናትና አባት) አባሉ በደንቡ መሰረት ካስመዘገባቸው የእድሩ ተጠቃሚዎች ናቸው:: ይሁን እንጂ ወላጆች በሚመዘገቡበት ወቅት ለእያንዳንዱ ወላጅ ለአንድ ጊዜ ብቻ የመመዝገቢያ እና የአባልነት ክፍያ መቶ ሀያ አምስት ዶላር($125) እየከፈሉ የአባሉ ጥገኛ ሆነው ይመዘገባሉ::

*11.1.5* አንዳንድ ወላጆች ባሪዞና እስቴት ውስጥ ከአንድ በላይ ልጆች ሊኖሯዋቸው ይችላሉ::ይሁን እንጂ መመዝገብ የሚችሉት ባንድ ልጅ ሥር ብቻ ነው። በእድሩ የቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጽ የተመዘገቡ ወላጆች የሞት አደጋ ሲደርስባቸው ሙሉ አገልግሎት ይደረግላቸዋል::አንድአባል ወይም ቤተሰቡ በሞት ሲለይ ግን ጥገኛ ሆነው የተመዘገቡ የአባል ወላጆች መዋጮ አያዋጡም፤

*11.1.6* ጥገኛ ሆነው የተመዘገቡ የአባል ወላጆች ከእድሩ ሙሉ አገልግሎት የሚያገኙት፤የወላጆች አስከሬን ከአስመዘገባቸው አባል ቤት ከዚህ ከአሪዞና ስቴት ወይም ካሪዞና ውጭ በሚኖር አባል ቤት ወጥቶ የቀብሩ ስነ ስርዓት የሚፈጸም ወይም አስከሬኑ ወደ አገር ቤት የሚላክ ሲሆን ብቻ ነው:: ከዚህ ውጭ ለአባሉ የወላጆች ሞት መርዶ ይሆናል:: እድሩ ደግሞ መርዶ አያስተናግድም::

## አንቀጽ 12: የእድር አባል በሞት መለየትን ስለማሳወቅ!

12.1 አንድ አባል ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ወይም ከቤተሰብ አባላት መሃል አንዱ ለእድሩ ጽ/ቤት፤ ለሰብሳቢው፣ ለም/ሰብሳቢው፣ ለጸሐፊው

ወይም ለቡድን መሪው፤ በአካል በመገኘት፣ ስልክ በመደወል፣ ቴክስት በማድረግ ወይም በኢሜይል ማሳወቅ ይጠበቅበታል::

12.2 አባሉ የሞተው በአሪዞና ስቴት ወይም በሌሎቹ የሰሜን አሜሪካ ስቴቶች ውስጥ ከሆነ የእድሩ አባል ቤተሰብ ፤ባል/ሚስት ወይም ልጅ ወይም ህጋዊ ተወካይ በሠላሳ (30) ቀናት ውስጥ ለእድሩ ጽሕፈት ቤት ማሳወቅ አለባቸው:: ከተሰጠው የጊዜ ገደብ ውጪ ከ30 (ሠላሳ) ቀን በኋላ የሚቀርብን ጥያቄ እድሩ አያስተናግድም። ምንም አይነት ክፍያ አይፈጽምም።

12.3 የአባሉ ቀብር ሥነስርዓት ከአሪዞና ስቴት ውጪ በሌሎች ስቴቶች ከተፈጸመ ዴዝ ሰርትፊኬት ( Death certificate) መቅረብ አለበት።

12.4 አባሉ የሞተው ከአሜሪካን ውጭ ከሆነ በዘጠና ቀናት ውስጥ ቤተሰብ ወይም ህጋዊ ተወካዩ የመሞቱን ሪፖርት ለእድሩ አመራር መግለጽ አለበት:: መሞቱንም የሚያረጋግጥ የሐኪም መረጃ (Death cirtificat) ማቅረብ አለበት፤ የሚያቀርበውም መረጃ ሕጋዊነቱን በሀገሪቱ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት በማህተም ተረጋግጦ መቅረብ አለበት::ይህ መረጃ ተሟልቶ ሲቀርብ ክፍያው ወዲያውኑ ይፈጸማል። ይህም ሊሆን የሚችለው በተሰጠው በዘጠና ቀናት ውስጥ ለእድሩ አመራር ጥያቄውን ማቅረብ ከቻለ ነው። ከተሰጠው ከጊዜ ገደብ ውጭ ለሚቀርብ ጥያቄ እድሩ ምንም አይነት ክፍያ አይፈጽምም፤ምንም ዓይነት አገልግሎት አይሰጥም።ይሁን እንጂ ሰነድ ለማቅረብ የጊዜ እጥረት ከገጠመ ጥያቄውን ለእድሩ አመራር በወቅቱ አቅርቦ የሰነድ ማቅረቢያ ተጨማሪ ጊዜ ሊጠይቅ ይችላል።

## አንቀጽ 13.ቅሬታና አለመግባባት የሚፈታበት ዘዴ

13.1 ያባላቱ መብት፤ ግዴታና ጥቅም የሚጠበቀውን የሚፈታው በዚህ ደንብ ብቻ ነው።

13.2 በእድሩ አሠራር ወይም በሚሰጡ ውሳኔዎች አባሉ ቅር ቢሰኝ ወይም አለመግባባቶች ቢፈጠሩ ችግሮቹ የሚፈቱት የዕድሩ አቃቤ ድንብ በሚሰይማቸው ሁለት ሽማግሌዎችና ባለጉዳዩ በሚሰይመው አንድ የኢትዮጵያውያንን የእድር ባሕልና ዓላማ ግንዛቤ ባለው ሽማግሌ ብቻ ነው።

13.3 ቅሬታን ወደ ፍርድ ቤት ማድረስ/መውሰድ አይቻልም።

13.4 ይህን የዕድር ደንብ ያልተቀበለ/ያልተቀበለች ግለሰብ የእድሩ አባል ሆኖ/ሆና መመዝገብ አይችልም/አትችልም።

### *አንቀጽ 14: የእድሩ መዋቅር*

14.1 የእድሩ የአወሳሰንና የአስተዳድር መዋቅር እንደሚከተለው ይሆናል።

14.1.1 ጠቅላላ ጉባኤ

14.1.2 አቃቢ ደንብ

14.1.3 የሥራ አመራር ኮሚቴ

14.1.4 ኦዲተርስ (ተቆጣጣሪዎች)

### አንቀጽ 15. የእድሩ ጠቅላላ ጉባዔ ሐላፊነት እና ተግባር

15.1 ጠቅላላ ጉባኤው የእድሩ የበላይ እና የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ አካል ነው። ስለሆነም ጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ ነው:: ከጠቅላላ ጉባኤው በላይ ይግባኝ ሰሚ አካል አይኖርም::

15.2 ጠቅላላ ጉባኤው በዓመት አንድ ጊዜ በእድሩ አመራር ኮሚቴ ዓመታዊ ስብሰባ ሲጠራ ይሰበሰባል::

15.3 ከአመራር ኮሚቴው የሚቀርበውን አጀንዳ አድምጦ ያጸድቃል:: በቅደም ተከተል አስቀምጦ በዝርዝር ይወያይበታል::ውሳኔም ይሰጣል::

15.4 ከእድሩ አመራር ኮሚቴ ሰብሳቢ የሚቀርበውን ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት እና በእድሩ ኦዲተር (ተቆጣጣሪ) የሚቀርበውን ሪፖርት ያዳምጣል፤ያሻሽላል፤ ያጸድቃል፡ መመሪያም ይሰጣል።

15.5 ሦስት የአስመራጭ ኮሚቴ አባልትን ሠይሞ የአመራር አባላት ምርጫ በደንቡ መሰረት እንዲፈጸም ያደርጋል:: የአስመራጭ ኮሚቴ መመሪያ በአመራሩ ተዘጋጅቶ ይቀርባል።

15.6 በየሁለት ዓመቱ የአገልግሎት ዘመኑን የሚፈጽመውን አመራር ኮሚቴ በክብር ያሰናብታል::ተረካቢውን የአመራር ኮሚቴ አባላት መርጦ ይሰይማል::

15.7 ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ያልቻሉ የአመራር አባላትን ያሰናብታል፤ በቦታቸውም ተተኪ አመራር አባላትን መርጦ ይመድባል::

15.8 የእድሩ ገቢ የሚያድግበትን መንገድ ከአመራር ኮሚቴ ጋር በመወያየት ጥናት እንዲቀርብ ያደርጋል:: የቀረበውንም ጥናት መርምሮ ያፀድቃል፤ ያሻሽላል፤ ሊሽርም ይችላል::

15.9 የእድሩን በጀት(ለሞትአደጋየሚከፈለውን የገንዘብ መጠን) ይመድባል፣ ያሻሽላል፣ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል::

15.10 የእድሩን ዓላማ ሊያዳብሩ አሰራሩንም ሊያጎለብቱ የሚችሉ እቅዶችንና ፖሊሲዎችን በአመራሩ እንዲዘጋጁ ያበረታታል ::

15.11 የጠቅላላ አባላት መደበኛ ጉባኤ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ቢሆንም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የእድሩ አመራር አስቸኳይ ስብሰባዎችን ሊጠራ ይችላል።

### አንቀጽ 16. *የእድሩ አቃቢ ደንብ*

16.1 የእድሩ አቃቤ ደንብ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ነው።

16.2 የአቃቤ ደንቡ አባላት ቁጥር ሦስት ሲሆን ሁለቱ ሁሌ ከመስራች አባላት መኃል ብቻ እየተመረጡ የሚሰየሙ ሲሆኑ ፤ የኮሚቴውም

ሰብሳቢ ከሁለቱ አንዱ ይሆናል። ሦስተኛው አባል ከጠቅላላ ጉባኤው መኃል የሚመረጥ የአቃቤ ደንቡ ጸሀፊ ሆኖ ያገለግላል።

16.3 የአቃቤ ደንቡ የአገልግሎት ዘመን ሦስት ዓመት ሆኖ የእድሩን ዓላማና ደንብ የማስከበር ተልእኮን መሰረት አድርጎ የሚከተሉት ኃላፊነቶችን እና ተግባራትን ያከናውናል።

16.3.1 የዕድሩ መተዳደሪያ ደንብ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ፤የአባላት መብትና ጥቅም ሳይሸራረፍ በተሟላ ሁኔታ ሁሉም አባላት እኩል እየተስተናገዱ መሆኑን ይታዘባል። የዘመመ አሰራር ሲከሰት ከአመራር አባላት ጋር በመነጋገር ችግሩ እንዲፈታ ምክር ይሰጣል። ችግሩ ከአልተፈታ ለጠቅላላ ጉባኤ እንዲቀርብ ያደርጋል።

16.3.2 የእድሩን ሕልውና የሚፈታተኑ ክስተቶች ከታዩ ከእድሩ አመራር አባላት ጋር በመሆን ችግሩ እንዲፈታ ያደርጋል። በዚህ ሁኔታ ሊፈታ ካልቻል በአስቸኳይ ለጠቅላላ ጉባኤው እንዲቀርብ ያደርጋል።

16.3.3 በመረዳጃ እድሩ አመራር አባላት መካከል ያስተሳሰብ; ያመለካከት ልዩነት ተፈጥሮ የእድሩን አሰራር የሚያደናቅፍ ፤ እድሩ የተቋቋመበትን ዋና ዓላማ የሚያስት ወይም የሚያሰናክል ሆኖ ከተገኘ እንደ አመችነቱ አባላትን በተናጠልም ሆነ በጋራ በማወያየት ችግሩ እንዲፈታ ይሸመግላል። ችግሩ በዚህ መልኩ ካልተወገደ ፤ አቃቤ ደንቡ ጠቅላላ ጉባኤውን በመወከል ሽማጊሌዎች ሰይሞ ጉዳዩ እንዲታይ ያደርጋል። በዚህ መልኩ ችግሩ ካልተፈታ በአስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ እንዲጠራ ያደርጋል። በአመራር በኩል ለጠቅላላ ጉባኤውም እንዲቀርብ ያደርጋል።

16.3.4 የእድሩ ሰብሳቢ ወይም ከአመራር አባላት መካከል ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የሚያደርጉትን ግንኙነቶች ጤነኛ ግንኙነት መሆኑን ይከታተላል። የእድሩን ዓላማ የሚጻረር ሆኖ ከአገኘው ግንኙነቱ እንዲቋረጥ ይጠይቃል። ያስፈጽማልም።

16.3.5 በእድሩ ውስጥ በአባላት ወይም በአመራር አባላት መካከል የፖለቲካ፡ የሐይማኖት፤ የጎሳ፤ የጎጥና የጾታ ልዩነቶችን የሚያንጸባርቅ ወይም የሚያንጸባርቁ ግለሰቦች ቢከሰቱ በእንጭጩ እንዲቀጭ ምክር ይሰጣል።

## *አንቀጽ 17. የእድሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ*

17.1 የአንድነት መረዳጃ እድር አመራር አካል በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጡ ዘጠኝ አባላት ያሉት የሥራ አመራር ኮሚቴ ይኖረዋል። እነሱም ሰብሳቢ፤ ምክትል ሰብሳቢ፤ ዋና ፀሐፊ፤ ምክትል ፀሀፊ፤ ገንዘብ ያዥ፤ ሂሳብ ሹም፤ ሦስት የእድሩ አባላት ይሆናሉ።

17.2 የሥራ አመራር ኮሚቴው እንደግልም አንደ ኮሚቴም ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ሲሆን የእድሩን የእለት ተዕለት እንቅስቃሴ /ሥራ/ በበላይነት ይመራል::

## አንቀጽ 18: የእድሩ ሰብሳቢ ኃላፊነትና ተግባር

18.1 የእድሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ሰብሳቢ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ሆኖ የእድሩ የበላይ ሐላፊ እና ተጠሪ ነው::

18.2 የእድሩ የመተዳሪያ ድንብ በትክክል ሳይዛባ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል::

18.3 የእድሩ አባላት ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ አመራር ይሰጣል:: ተገቢውንም አገልግሎት እያገኙ መሆኑን ያረጋጋጣል::

18.4 የእድሩን አመራር አባላት ያስተባብራል:: ይመራል:: ገንዘብ ወጭ እንዲደረግ በገንዘብ ወጪ ማዘዣ ላይ ፈርሞ ወጪ ያዛል:: በወጪ ቼክ ላይ ከገንዘብ ያዡ ጋር ይፈርማል።

18.5 የእድሩን ዓላማ በአግባቡ ለማራመድ እንዲቻል ሊያገለግሉ የሚችሉ የቡድን መሪዎች በደንቡ መሰረት እንዲቋቋሙ ያደርጋል። ለሚቋቋሙት የቡድን መሪዎች ***/ረዳት ገንዘብ ሰብሳቢዎች/*** የተቋቋሙበትን ዓላማ ለማከናወን የሚያስችል መመሪያ /የሥራ ድርሻ/ እንዲዘጋጅ ያደርጋል::

18.6 በዓመት አንድ ጊዜ በደንቡ ላይ በተደነገገው ቀን ቦታ እና ሠዓት የእድሩን ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ይጠራል:: ስብሰባውን ይመራል:: ሁለገብ ሪፖርትም ያቀርባል::ከጠቅላላ ጉባዔ የሚሰጡትን ውሳኔዎች ያከብራል:: ሥራ ላይም ያውላል:: መዋላቸውንም ይከታተላል::

18.7 ከእድሩ አመራር አባላት መሃል ሐላፊነቱን በብቃት፣ በትጋት የማይወጣ፤ እድሩ ለአባላት የሚያበረክተውን አገልግሎት የሚያዳክም፣ በተደጋጋሚ በስብሰባ የማይገኝ፣ ሰዓት የማያከብር፣ ለማዕከላዊ አሰራር የማይገዛ አመራር አባል ሲከሰት ለእድሩ አመራር አቅርቦ፣ ቃለ ጉባኤ ተይዞ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል::

18.8 ሃላፊነቱን በሚገባ በማይወጣ የአመራር አባል ላይ የሚወሰደው የእርምት እርምጃ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ ይሆናል:: ይኸውም፡-

18.7.1 ለመጀመሪያ ምክር አዘል የቃል መስጠንቀቂያ፤

18.7.2 ለሁለተኛ ጊዜ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፤

18.7.3 ለሦስተኛ ጊዜ በፅሁፍ ከሃላፊነት እንዲነሳና በቦታውም በሌላ አባል እንዲተካ ያደረጋል::

18.9 ከአባላት የሚሰበሰበው መዋጮ በተገቢው ሁኔታ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተሰብስቦ ባንክ አካውንት መግባቱን ያረጋግጣል::

18.10 በአባላት ወይም በቤተሰቦቻቸው ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ በደንቡ መሰረት ገንዘብ ከእድሩ አካውንት በአስቸኳይ ወጭ ተደርጎ አደጋ

ለደረሰበት አባል ህጋዊ ተወካይ ወይም ቤተሰብ እንዲደርስ አስፈላጊውን አመራር ይሰጣል::

18.11 የእድሩ ሂሳብ ሹም የወጪ ማዘዣ አዘጋጅቶ ሲያቀርብለት በወጪ ማዘዣ ሰነድ ላይ ፈርሞ ወጪ ተደርጎ እንዲከፈል ለገንዘብ ያዡ መመሪያ ይሰጣል:: የእድሩ የባንክ አካውንት በቼክ ብቻ መንቀሳቀሱን ይቆጣጠራል:: ያረጋግጣልም::

18.12 ለእያንዳንዱ አባል የግል ፋይል ተከፍቶ ማንኛውም አባሉን የሚመለከት መረጃ /ከእድሩ ጋር ባለው ግንኙነት/ ተመዝግቦ እንዲቀመጥ ለጽህፈት ቤቱ መመሪያ ይሰጣል::

18.13 አባሉ እና ቤተሰቡ በእድሩ የአባልነት መመዝገቢያ ቅጽ 3 (ሦስት) በአግባቡ ተሞልቶ በፋይል ውስጥ ተያይዞ መቀመጡን ያረጋግጣል:: ይቆጣጠራል: በሞት ወይም አካባቢውን በመልቀቅ የሚለይ አባል ወይም የአባል ቤተሰብ ካለ በወቅቱ ከእድሩ መዝገብ እንዲሰረዝ ያደርጋል:

18.14 የእድሩ ገንዘብ እንቅስቃሴ በደንቡ መሠረት እየተካሄደ መሆኑን ያለሰለሰ ክትትል ያደርጋል።

18.15 የእድሩን አመራር አባላት በየ 3 ወሩ እየሰበሰበ የእድሩን እንቅስቃሴ እንዲገመገም ያደርጋል:: የእድሩ አሰራር የሚዳብርበትን እና ለአባላትም ተገቢ አገልግሎት ሊያበረክት የሚችልበት ሁኔታ እንዲጎለብት አዳዲስ ሃሳቦች እና አሰራሮች እንዲፈጠሩ ያደርጋል::

18.16 በአመራር አባላት መሃል ያመለካከት /የሃሳብ/ ልዩነት ተፈጥሮ የእድሩን ሥራ የሚያደናቅፍ ሁኔታ ሲከሰት አስቸኳይ የአመራር አባላትን ስብሰባ ጠርቶ ዲሞክራሲያዊ በሆነ አካሄድ ችግሩ እንዲፈታ ያደርጋል::

18.17 ለእድሩ አመራር አባላት እና ለእድሩ አቃቤ ደንብ በማማከር ድጋፍ ከአገኘ እድሩን ወክሎ በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ ሊሳተፍ ይችላል። ድጋፍ ካላገኘ ግን መሳተፍ አይችልም::

18.18 የስራ አመራር ኮሚቴ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት እድሩን ወክሎ ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር የሥራ ግንኙነት ሊያደርግ ይችላል።

## <u>አንቀጽ 19፡ ምክትል ሰብሳቢ ሃላፊነትና ተግባር</u>

19.1 ም/ሰብሳቢው ተጠሪነቱ ለእድሩ ሰብሳቢ ሆኖ ሰብሳቢው በማይገኝበት ወቅት ሰብሳቢውን ተክቶ ይሰራል።የሰብሳቢውንም ሙሉ ስልጣንና ኃላፊነት ይጠቀማል።

19.2 የእድሩን የቡድን መሪዎች ያስተባብራል፣ በየወቅቱ እንደአስፈላጊነቱ የቡድን መሪዎችን እንቅስቃሴ እየገመገመ ለሰብሳቢው ሪፖርት ያቀርባል::

19.3 የእድሩ ሰብሳቢ የእድሩን ሥራ አስመልክቶ የሚሰጠውን ማንኛውንም ሥራ ይሰራል::

19.4 የእድሩ ዋና ፀሐፊ በማይኖርበት ጊዜ ለም/ፀሐፊው ድጋፍ በማድረግ የጽህፈት ሥራው በአግባቡ እንዲሠራ ያደርጋል::

## <u>አንቀጽ 20: የእድሩ ዋና ፀሃፊ ሃላፊነትና ተግባር</u>

የእድሩ ዋና ፀሐፊ ተጠሪነቱ ለእድሩ ሰብሳቢ ሆኖ የሚከተሉት ሐላፊነቶች ይኖሩታል::

20.1 የእድሩ ዋና ፀሐፊ የጠቅላላ ጉባዔው እና የእድሩ አመራር ኮሚቴ ፀሐፊ ነው

20.2 የእድሩን ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባም ሆነ የእድሩ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ ወቅትቃለ ጉባዔ ይይዛል:: ቃለ ጉባኤውን በስብሰባው የተሳተፉትን አባላት አ ስፈርሞ በጥንቃቄ ያስቀምጣል።

20.3 ፀሐፊው የእድሩን ጽ/ቤት ይመራል:: የጽህፈት ሥራውን በኃላፊነት ይሰራል።

20.4 ገቢና ወጪ ደብዳቤዎችን በሰነድ ላይ እየመዘገበ በጥንቃቄ ይይዛል።

20.5 ሰብሳቢው እና ም/ሰብሳቢው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከምድብ ሥራቸው ላይ መገኘት በማይችሉበት ወቅት የሰብሳቢውን ሙሉ ስልጣን በመጠቀም እድሩን በሃላፊነት ይመራል:: ሰብሳቢውና ም/ሰብሳቢው ከ6 ወር በላይ ከምድብ ሥራቸው ላይ መገኘት ካልቻሉ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ጠርቶ በቦታቸው ሌሎች አባላት ተመርጠው እንዲተኩ ያደርጋል።

20.6 የአገልግሎት ዘመኑን አጠናቆ ሐላፊነቱን ለተተኪው አመራር አባል ሲያስረክብ በእጁ ላይ የሚገኙትን የእድሩን ሰነዶች እና ንብረቶች በሙሉ መዝግቦ ርክክቡ በሰነድ እንዲፈፀም ያደርጋል::

20.4 የእድሩን አባላት ስም ዝርዝር፣ አድራሻና ልዩ ልዩ መረጃዎችን መዝግቦ በጥንቃቄ ይይዛል/ያስቀምጣል::የእድሩ አባል ለመሆን ጥያቄ የሚያቀርቡ ግለሰቦችን የመጠየቂያ ፎርሙን ሞልተው ሲያቀርቡለት ተቀብሎ ለአመራር አባላት አቅርቦ ያስወስናል::

20.5 በተጨማሪም ከሰብሳቢው እና ከም/ሰብሳቢው የሚሰጠውን ማንኛውንም የእድሩን ሥራ በሙሉ ይሠራል::

## <u>አንቀጽ 21: የእድሩ ም/ፀሐፊ ሃላፊነትና ተግባር</u>

የእድሩ ም/ፀሐፊ ተጠሪነቱ ለእድሩ ሰብሳቢ ሆኖ የሚከተለው ተግባር እና ሐላፊነት አለው::

21.2 ከእድሩ ዋና ፀሐፊ ጋር በመተባበር የእድሩን የፅህፈት ሥራ ይሰራል::

21.3 የእድሩ ዋና ፀሐፊ በማይኖርበት ወቅት ዋና ፀሐፊውን ተክቶ የፀሐፊውን ሙሉ ስልጣን በመጠቀም የፅህፈት ሥራውን ያከናውናል::

21.4 የእድሩ የሕዝብ ግንኙነት ሐላፊ ሆኖ ይሰራል። የስራ ድርሻው በሚፈቅደው መሰረትሀላፊነቱንይወጣል።ም/ጸሀፊው በተጨማሪም

የአንድነት መረዳጃ እድር ዋና እቃ ግዢ እና የንብርት ሀላፊነትን ደርቦ ይሰራል።

## አንቀጽ 22፡ የእድሩ ገንዘብ ያዥ ሃላፊነትና ተግባር

የእድሩ ገንዘብ ያዥ ተጠሪነቱ ለእድሩ ሰብሳቢ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራት እና ኃላፊነቶች አሉት::

22.1 ከአባላት የሚሰበሰበውን መዋጮ በወቅቱ ይሰበስባል ። የቡድን መሪዎችም በወቅቱ ክፍያውን መሰብሰባቸውን እና የተሰበሰበው ገንዘብ በአምስት ቀናት ውስጥ ባንክ ማስገባታቸውን ይከታተላል ።ወይንም ገንዘቡን ከቡድን መሪዎች በሰነድ ተረክቦ ባንክ ገቢ ያደርጋል።

22.2 ከሂሳብ ሹሙ ተመዝግቦ በሚሰጠው የእድሩ ሕጋዊ የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብቻ ገንዘብ ይሰበስባል:: የእድሩም አባል ወይም አባላት በእድሩ ባንክ አካውንት መዋጮውን ገቢ ማድረጉን/ማድረጋቸውን ካረጋገጠ በኋላ የእድሩን ህጋዊ ደረሰኝ ይሰጣል::

22.3 ገንዘብ ወጪ እንዲደረግ በሒሳብ ሹሙ ሕጋዊ ሰነድ ተዘጋጅቶ የእድሩ ሰብሳቢና ሒሳብ ሹሙ ፈርመውበት ገንዘብ ወጭ እንዲደረግ ሲታዘዝ፤ ሒሳብ ሹሙ ወጪ እንዲሆን፤ የታዘዘውን የገንዘብ መጠን በቼክ ላይ ጽፎ የእድሩን ሰብሳቢ አስፈርሞ የወጪ ማዘዣውን እና ሰብሳቢው የፈረሙብትን ቼክ አያይዞ ለገንዘብ ያዡ ሲያቀርብ ሰብሳቢው በሁለቱም በወጪ ማዘዣው እና በቸክ ላይ መፈረሙን ካረጋገጠ በኋላ የወጪ ማዘዣውን እና ቸኩን ተረክቦ እሱም በቸኩ ላይ ፈርሞ ክፍያ ይፈጽማል::ማንኛውም ክፍያ የሚፈጸመው በሁለት የአመራር አባላት ፊርማ በቼክ ብቻ ነው።በቼክ ላይ የሚፈርሙ ሰብሳቢው እና ገንዘብ ያዡ ናቸው። ገንዘብ ያዡ ከሌለ፤ ሰብሳቢው እና ም/ሰብሳቢው ፈርመው ክፍያ ይፈጽማሉ። ሰብሳቢው ከሌለ ም/ሰብሳቢው እና ገንዘብ ያዢው ቼክ ላይ ፈርመው ክፍያ ይፈጽማሉ። በአንድ ሰው ፊርማ ብቻ ከባንክ ገንዘብ ማውጣት ክፍያ መፈጸም በፍጹም አይቻልም።

22.4 ገንዘብ ያዡ የእድሩን ሂሳብ ሊያንቀሳቅስ የሚችለው በቼክ ብቻ ነው። ጥሬ ገንዘብ ባንክ ሳይገባ አንድ ዶላር እንኳ ወጪ ሊያደርግ አይችልም።

22.5 ከሂሳብ ሹሙ ፈርሞ የሚረከበው ሕጋዊ የገንዘብ መሰብሰቢያ ጥራዝ ባለ ሦስት ኮፒ ደረሰኝ ሲሆን፤ ገንዘብ ሲሰበስብ ዋናውን ኮፒ ለገንዘብ ከፋይ፤ ሁለተኛውን ኮፒ ለሂሳብ ሹም፤ ሦስተኛው ኮፒ ከጥራዙ ጋር እንደተያያዘ በእጁአቆይቶ ለኦዲተሩ ያቀርባል:: የሂሳብ ምርመራም ይደረግበታል::

22.6 ማንኛውየወጪምሆነየገቢሰነዶችየተሰራባቸውንምያልተሰራባቸውንምሰነዶች በጥንቃቄ ያስቀምጣል:: በሂሳብ ሹሙና በኦዲተር ሲጠየቅ ያቀርባል::

22.7 የገቢ እና የወጭ መዛግብት አዘጋጅቶ የእለቱን ገቢ ከነምንጮቹ ወጭውንም ከነምክንያቱ እየመዘገበ በጥንቃቄ ይይዛል::

## አንቀጽ 23: የእድሩ ሂሳብ ሹም ሃላፊነትና ተግባር

የእድሩ ሂሳብ ሹም ተጠሪነቱ ለእድሩ ሰብሳቢ ሆኖ የሚከተሉት ኃላፊነቶች እና ተግባራት ይኖሩታል።

23.1 ከአባላት የሚሰበሰበው የመመዝገቢያም ሆነ የአባልነት ክፍያና በአንድ የእድር አባል ወይም በቤተሰቡ ላይ አደጋ ደርሶ ገንዘብ ከእድሩ ባንክ አካውንት ወጭ ሆኖ ከተከፈለ በኋላ የወጣውን ገንዘብ መልሶ ባንክ ለማስገባት እያንዳንዱ አባል ድርሻውን በእድሩ ደንብ መሠረት በሕጋዊ ደረሰኝ ገቢ ማድረጉን እና በወቅቱ ባንክ ገቢ መሆኑን ይከታተላል:: ያረጋግጣል::

23.2 ተከታታይ ቁጥር ያላቸው የገንዘብ መሰብሰቢያና ልዩ ልዩ ሰነዶችን በእድሩ ስም እንዲዘጋጅ ያደርጋል/ያሳትማል።

23.3 የእድሩ የገንዘብ መሰብሰቢያ ሕጋዊ ደረሰኝ እያንዳንዱ ጥራዝ በሦስት ኮፒ ተዘጋጅቶ ከቁጥር አንድ (1) እስከ መቶ ቁጥር (100) ተብሎ እየተመዘገበ ለገንዘብ ያዡ እና ለቡድን መሪዎች እያስፈረመ ይሰጣል። ተሰርቶበት ሲያልቅም ተጨማሪ እየመዘገበ እና እያስፈረመ ይሰጣል:: ያልተሰራባቸውን ጥራዞችንም በጥንቃቄ ያስቀምጣል::

23.4 የቡድን መሪዎች ህጋዊ ገንዘብ ሰብሳቢዎች ናቸውና ሦስት ኮፒ ባለው ሕጋዊ ደረሰኝ ገንዘብ መሰብሰባቸውን፤ 1ኛውን ኮፒ /ዋናውን ኮፒ/ ለገንዘብ ከፋይ፤ 2ኛውን ኮፒ ለሒሳብ ሹሙ፤ 3ኛውን ኮፒ ከጥራዝ ሳይገነጠል እንደተያያዘ በቡድን መሪዎች እጅ መኖሩን ይከታተላል። ያረጋግጣል::

23.6 በየወሩ ከባንክ የሚላከውን ባንክ ስቴትመንት በጥንቃቄ በቅደም ተከተል እየመዘገብ ያስቀምጣል::

23.7 ለእድር አባላት የእርዳታውን ገንዘብ በእለቱ እንዲደርስ አስፈላጊውን ሁሉ በማድረግ ሐላፊነቱን ይወጣል::

23.8 የእድሩ ሰብሳቢ የሚሰጠውን ማንኛውንም ሒሳብ ነክ ሥራ ይሰራል:: የሰነዶችን የማሳተም (የህትመት) ሥራ ሃላፊነትም የሂሳብ ሹሙ ነው::

23.9 የመረዳጃ እድሩን የገንዘብ እንቅስቃሴ ገቢና ወጪ ኮምፒውተር ላይ በመመዝገብ በየጊዜው ፓወር ፖይንት እያዘጋጀ ለአመራሩ የተሟላ የሂሳብ መረጃ ያቀርባል።

## አንቀጽ 24: የእድሩ የውስጥ ተቆጣጣሪ/ኦዲተር/ ሃላፊነትና ተግባር

24.1 የእድሩ ኦዲተር ሦስት (3) አባላት ያሉት ሲሆን፤ ተጠሪነቱ ለእድሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ የሚከተሉት ኃላፊነቶች፤ ተግባራትና ስልጣን አለው።

24.2 የእድሩ ንብረት ለእድሩ አገልግሎት ብቻ መዋሉን ይቆጣጠራል::

24.3 አባላት የድርሻቸውን መዋጮ በወቅቱ ገቢ ማድረጋቸውን ይቆጣጠራል::

24.4 አባላት ሲመዘገቡ ቤተሰቦቻቸውንም ሲያስመዘግቡ በእድሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት መፈጸሙን ያረጋግጣል::

24.5 የባንክ አካውንት ተከፍቶ የእድሩ ገንዘብ በወቅቱ ባንክ መግባቱን ይቆጣጠራል:: ከአባላት የሚሰበሰበውም ገንዘብ በአምስት ቀናት ውስጥ ባንክ መግባቱን ያረጋግጣል::

24.6 የእድሩ ሂሳብ ሹም ከአባላት የሚሰበሰበው መዋጮ በህጋዊ ደረሰኝ እንዲሰበሰብ ህጋዊ ደረሰኝ አሳትሞ ሲያከፋፍል፤ የታተሙትን ጥራዞች በሙሉ በቅደም ተከተል ቁጥር የታተሙና የተመዘገቡ መሆናቸውን ይቆጣጠራል።

24.7 ለገንዘብ ያዡ እና ለቡድን መሪዎች ጥራዝ ደረሰኞች ሲሰጡ ቁጥሮች በቅደም ተከተል የተመዘገቡ መሆናቸውን፤ ገንዘብ ተቀባዮችም እየፈረሙ መረከባቸውን ይቆጣጠራል።

24.8 አባላት ከእድሩ ተገቢውን አገልግሎት እያገኙ መሆንን ያረጋግጣል።

24.9 የአባላት መመዝገቢያ ቅጽ በወቅቱ በአግባቡ ተሞልቶ በፋይል ተያይዞ መቀመጡን ይቆጣጠራል::

24.10 ኦዲተሩ ለጠቅላላ ጉባኤ የሚያቀርበውን ማንኛውንም ሪፖርት ቅጂ አንድ ኮፒ ለሥራ አሥፈጻሚ ኮሚቴ ከአሥር ቀናት በፊት ቀደም ብሎ መስጠት አለበት። ሥራ አስፈጻሚውም ሪፖርቱን አስመልክቶ ለሚያቀርብለት ጥያቄ ማብራሪያ የመስጠት ግዴታ አለበት። ኮፒው ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያልቀረበ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤ ሊቀርብ ይችላል።

24.11 የእድሩ አመራር የእድሩን እንቅስቃሴ /አሰራር/ በደንቡ መሠረት እየሰሩ /እያከናወኑ/ መሆኑን እና የእድሩም ደንብ በአፈጻጸም ያልተጣሰ መሆኑን በቅርብ ይከታተላል::

24.12 ኦዲተሩ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር በእድሩ አመራር ስብሰባ ላይ ሊገኝ አይገባውም:: በአመራር ስብሰባ ላይ መገኘት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ፤ ሃሳብ መስጠት፣ ጥያቄ እና ማብራሪያ መጠየቅ ይችላል:: የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ፣ ድምጽ መስጠት፣ መደገፍ እና መቃወምም ፈጽሞ አይችልም::

24.13 ኦዲተሩ ያለምንም የአመራር ተጽዕኖ እና ጣልቃ ገብነት በነጻ የምርመራ ሥራውን ያከናውናል::

24.14 ኦዲተር የአጭር እና የረጅም ጊዜ የስራ እቅድ አዘጋጅቶ አንድ ኮፒ ለእድሩ አመራር ሰጥቶ ሥራውን ግን ያለማንም ጣልቃ ገብነት በእቅዱ መሰረት ያከናውናል::

24.15 የእድሩ ገንዘብ አሰባሰብ፣ አያያዝ እና አወጣጥ/አጠቃቀም/ በእድሩ ደንብ መሠረት መፈጸሙን ይቆጣጠራል::

24.16 ኦዲተሩ በአንድ አባል ቤት አደጋ ደርሶ እድሩ ኃላፊነቱን ከተወጣ በ30 ቀናት ውስጥ የእድሩን አመራር የሥራ እንቅስቃሴ ይገመግማል:: መሰብሰብ ያለበት መዋጮ ደንቡ በሚፈቅደው የጊዜ ገደብ መሠረት ተሰብስቦ ገቢ መሆኑን ይከታተላል::

24.17 ኦዲተሩ በዓመት አንድ ጊዜ የእድሩን የሥራ እንቅስቃሴ እና የገንዘብ አያያዝ በዝርዝር ለጠቅላላ ጉባዔው አመታዊ ሪፖርት ያቀርባል::

24.18 ኦዲተሩ አባላት መብታቸው እና ጥቅማቸው ሳይሸራረፍ እያገኙ መሆኑን ያረጋግጣል:: በአመራር መሃል የአሰራር ድክመት ሲከሰት በአስቸኳይ እንዲታረም ለእድሩ አመራር ሃሳብ ያቀርባል፣ መስተካከሉንም ይከታተላል:: ለጠቅላላ ጉባኤውም በሪፖርት ያቀርባል።

24.19 ኦዲተሩ በማንኛውም ወቅት ለኦዲት መረጃ መጠየቅ እና ማግኘት ይችላል:: የተጠየቀውም አካል ያለምንም ማዘግየት የተጠየቀውን ሰነድ የማቅረብ ግዴታ አለበት::

24.20 የእድሩ አመራር ሰብሳቢ በቁጥጥር ሥራው ውስጥ ጣልቃ አይገባም እንጂ፤ የእድሩን አሰራር እና የፋይናንስ እንቅስቃሴ የገንዘብ አያያዝን እና አሰባሰብን አስመልክቶ ተጨማሪ ሥራ ሊሰጣቸው ይችላል:: ኦዲተሮቹም የተጠየቁትን ያለማመንታት የመፈጸም ግዴታ አለባቸው::

24.21 ሦስቱ ኦዲተሮች የሥራ ኃላፊነት ክፍፍል ያደርጋሉ። አንዱ ኦዲተር ዋና ኦዲተር ሆኖ የኦዲተሮች ሰብሳቢ ይሆናል። ከሁለቱ ኦዲተሮች መኃል አንዱ ጸሀፊ ሌላው አባል በመሆን ተመዳድበው የቁጥጥር ሥራቸውን ያከናውናሉ።

**<u>አንቀጽ 25: የቡድን መሪዎች</u>**

የቡድን መሪዎች ተጠሪነታቸው ለእድሩ ገንዘብ ያዥ ሆኖ የሚከተሉት ኃላፊነቶች እና ተግባራት ይኖሯቸዋል፡-

25.1 የእድሩ የቡድን መሪዎች ብዛት የሚወሰነው በአባላት ቁጥር ብዛት ይሆናል::

25.2 አንድ የቡድን መሪ በሥሩ ሠላሳ መደበኛ አባላት ይኖሩታል።

25.3 የእድሩ የቡድን መሪዎች ህጋዊ ገንዘብ ሰብሳቢዎች ስለሆኑ በሥራቸው ከተደራጁ አባላት መዋጮ ይሰበስባሉ።

25.4 አንድ የቡድን መሪ በስሩ የተዋቀሩትን አባላት

25.4.1 ሙሉ ስም

25.4.2 ሙሉ አድራሻ

25.4.3 ስልክ ቁጥር

25.4.4 የቤተሰብ ብዛት እና ዝምድናን የሚገልጽ ዝርዝር፤

25.4.5 በሥሩ የተዋቀሩ የእድሩ አባላት የሞሉት የቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጽ 3 በእያንዳንዱ አባል የተሞላውን ቅጽ አንድ ኮፒ መያዝ አለበት።

25.5 በስሩ የተዋቀሩ አባላት የሚከፍሉትን መዋጮ መጠን ከሂሳብ ሹሙ ወይም ከገንዘብ ያዡ መመሪያ ሲወርድለት በወቅቱ በሥሩ ለሚገኙ አባላት መክፈል የሚገባቸውን የገንዘብ መጠን እና የጊዜ ገደብ አሳውቆ ገቢ እንዲያደርጉ መመሪያ ይሰጣል። ይቀሰቅሳል ። ይከታተላል፣ በወቅቱ ገቢማድረጋቸውንም ይቆጣጠራል::

25.6 የቡድን መሪው በስሩ የተደራጁ አባላት በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ድርሻቸውን ገቢ ሳያደርጉ፤ የጊዜ ገደብ ያለፈባቸውን አባላት ስም ዝርዝር በአስቸኳይ ለም/ሰብሳቢው እና ለሂሳብ ሹሙ ያቀርባል:: ገቢ ያደረጉትን አባላት፤ ገቢ ያደረጉበትን የባንክ ሰነዳቸውን ሲያቀርቡ የእድሩን ሕጋዊ ደረሰኝ በመስጠት መከፈላቸውን ያረገግጣል:: አባላት ካሽ ወይም በቼክ ክፍያ ለመፈጸም ሲቀርቡ ወዲያውኑ የእድሩን ሕጋዊ ደረሰኝ እየሰጠ ገንዘቡን ይቀበላል:: በአምስት ቀናት ውስጥ ገንዘቡንም በድሩ ባንክ አካውንት ገቢ ያደርጋል::

**አንቀጽ 26: የአደጋ ወቅት ክፍያ መጠን**

26.1 የእድሩ አባላት ቁጥር ብዛት 150 ከደረሰ ለአባላት አገልግሎት መስጠት ይጀምራል:: የአባላት ብዛት መቶ ሀምሳ ለመሙላት ረዥም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ ፤ ጉዳዩን ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ በማስወሰን አገልግሎት መስጠት ይጀምራል።

26.2 የእድሩ መደበኛ አባላት ቁጥር 300 እስኪደርስ ድረስ በአንድ አባል ወይም በቤተሰቡ ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ $10,000 /አስር ሺ ዶላር/ በእለቱ ከእድሩ የባንክ አካውንት ወጪ እየተደረገ የቀብሩ ሥነስርዓት በወቅቱ ይፈጸማል::ከእድሩ የባንክ አካውንት ወጪ የተደረገውም $10,000 ዶላር በወቅቱ ባሉት የአባላት ቁጥር እኩል ተካፍሎ(ተመድቦ) እያንዳንዱ አባል ድርሻውን በእድሩ ደንብ ውስጥ በተደነገገው የክፍያ ማጠናቀቂያ የጊዜ ገደብ /በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ/ ገቢ ያደረጋል::

26.3 የእድሩ መደበኛ አባላት ቁጥር ብዛት ከ300 በላይ ሲሆን በአደጋ ጊዜ የሚከፈለው ክፍያ እስከ $15,000 /አስራ አምስት ሺህ/ ዶላር ሊደርስ ይችላል። ይህም በጠቅላላ ጉባዔ ከጸደቀ በኃላ ብቻ ነው::

**አንቀጽ 27: ተደራራቢ ወይም ተከታታይ የሞት አደጋ በደረሰ ጊዜ የክፍያ አፈጻጸም**

27.1 በአንድ ጊዜ በሁለት አባላት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ተከታታይ ወይም ተደራራቢ የሞት አደጋ ቢያጋጥም በእድሩ ደንብ መሰረት ለእያንዳንዱ አደጋ ሙሉ ክፍያ ይፈጸማል። እያንዳንዱ የእድር አባል የሚያዋጣው መዋጮ መጠኑ የእድሩ አመራር ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ሆኖ፤ እያንዳንዱ አባል መዋጮውን በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት። በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ መዋጮውን ገቢ የማያደርግ አባል የሃያ አምስት ዶላር ($25 ዶላር) ቅጣት ተጨምሮ በቀጣዩ አስራ አምስት ቀናት ውስጥ ገቢ ያደርጋል። ይህንን የማይፈጽም፤ ከእድሩ ይሰናበታል። ይሁን እንጂ ከአቅም በላይ የሆነ ጉዳይ ካጋጠመው አባሉ ጉዳዩን የጊዜ ገደቡ ከመድረሱ አስቀድሞ ለአመራር ኮሚቴ አባላት ያቀርባል። ተቀባይነት ካገኘ በቀጣዩ አሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ያለ ቅጣት አጠቃሎ ገቢ ማድረግ አለበት። ካላደረገ ግን በደንቡ መሰረት ከድሩ ይሰናበታል።

**አንቀጽ 28፡ በእድሩ አባል ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ ለጠቅላላ አባላት ስለማሳወቅ**

28.1 በአንድ አባል ወይም በእድሩ የአባላት መመዝገቢያ ቅጽ ላይ በተመዘገቡ የአባላት ቤተሰብ ላይ የሞት አደጋ መድረሱ እንደተሰማ ፤ የእድሩ ጽ/ቤት እና የቡድን መሪዎች በእለቱ ለጠቅላላ የእድሩ አባላት በስልክ፣ በቴክስት፣ በኢሜይል እና በሌሎችም ቴክኔዎሎጂ ወለድ መገናኛ ዘዴዎች መልእክት ያስተላልፋሉ::

**አንቀጽ 29: መዋጮ መክፈል ስለማይችሉ አባላት**.

29.1 የእድሩ አባላት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መዋጮ መክፈል የማይችሉባቸው ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ተቀባይነት ሊያገኙ የሚችሉ ምክንያቶች፣

29.1.1 አባሉ በህግ ጥበቃ ሥር የሚገኝ ከሆነ እና ከታሰረበት እስር ቤት በቂ የሆነ ሕጋዊ መረጃ ማቅረብ ከቻለ፤

29.1.2 አባሉ በወቅቱ በሆስፒታል ተኝቶ ህክምናውን እየተከታተለ ያለ ከሆነ፤ በህመሙ ምክንያት ገቢውም የተቋረጠ ከሆነ እና የህክምና ማስረጃ ማቅረብ ከቻለ ከክፍያ ነጻ ይሆናል፤ በአንቀጽ 29.1.1 እና በአንቀጽ29.1.2 በተገለጹት እና ተመሳሳይ ይዘት ባላቸው ሁኔታዎች ላይ የሚገኙ አባላት በወቅቱ በአንድ አባል ወይም በቤተሰቡ ላይ የሞት አደጋ ቢደርስ እያንዳንዱ አባል የሚያዋጣውን መዋጮ ማዋጣት አይጠበቅባቸውም:: ከመዋጮ ክፍያ ነጻ ይሆናሉ:: እነርሱ መክፈል የሚገባቸው መዋጮ ከእድሩ አካውንት ወጭ ተደርጎ ይሸፈናል፣ ወይም ለጠቅላላ አባላት ይከፋፈላል:: በዚህ አባል ወይም በቤተሰቡ ላይ የሞት አደጋ ከደርስ ግን ከእድሩ ተገቢውን ክፍይ ያገኛል::አደጋ ሲደርስ ከመዋጮ( ክፍያም) ነጻ የሚሆነውም፤ በእርሱ ላይ ሆነ በቤተሰቡ ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ ከእድሩ ተገቢውን አገልግሎት ማግኘት የሚችለውም አባሉ እክል ከገጠመው ለእድሩ ጽ/ቤት ማሳወቅ ከቻለ ብቻ ነው:: ይህን ካላደረገ ግን ከእድሩ ይሰናበታል:: ከዚህም የከፋ ችግር የሚያጋጥማቸው የእድሩ አባላት ሲኖሩ ለእድሩ አመራር ኮሚቴ ጉዳዩን በጽሁፍ ያቀርባሉ፤ አመራሩም ፈጣን ውሳኔ ይሰጣል።

**አንቀጽ 30፡ የሚሰበሰበውን መዋጮ በወቅቱ ስለማይከፍል አባል**

30.1 አንድ አባል በተሰጠው የጊዜ ገደብ መዋጮውን ገቢ ካላደረገ/በወቅቱ ካልከፈለ/ የሚከተለው ቅጣት ይፈፀምበታል።

30.2 አንድ አባል ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ በእድሩ መገናኛ ዘዴ ለእድሩ አባላት ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ መዋጮው ተጠቃሎ ገቢ መደረግ አለበት:: በተሰጠው የ15 ቀናት የጊዜ ገደብ ውስጥ አጠቃሎ መክፈል ያልቻለ የእድሩ አባል $25.00 ዶላር ቅጣት ተጨምሮ በቀጣዩ አስራ አምስት ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት:: መረጃው ከደረሰው ወይም ከተነገረው የመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ያለበቂ ምክንያት በ30 ቀናት ውስጥ የሚፈለግበትን ክፍያ ገቢ ሳያደርግ ከቀረ በ31ኛው ቀን ከእድሩ አባልነት ይሰረዛል:: ከዚህ ከሰላሳ አንድ ቀን (31 ቀን) በኋላ በእሱም ላይ ሆነ በቤተሰቡ ላይ የሞት አደጋ ቢደርስ ምንም አይነት የገንዘብም ሆነ የሌላ አገልግሎት አይደረግለትም፤ ምክንያቱም ከድሩ አባልነት ተሰናብቷልና።

30.3 ከእድሩ በጥፋትም ሆነ በፈቃዱ የተሰናበተ ቀድሞ የከፈላቸው የመመዝገቢያም ሆነ የአባልነት ክፍያ ተመላሽ አይደረግለትም፤ተመልሶ የእድሩ አባል ለመሆን በጽሁፍ ከጠየቀ ግን እንደ አዲስ አባል መመዝገቢያና የአባልነት ክፍያ ከፍሎ አባል መሆን ይችላል።

## አንቀጽ 31፡ የእድሩ አመራር አባላት በሕግ ተጠያቂ የሚሆኑበት እና የህግ ከለላ የሚያገኙበት

31.1 የአንድነት መረዳጃ እድር የሥራ አመራር ኮሜቴ አባላት እድሩ ከሚኖረው ከማንኛውም እዳ ወይም ሐላፊነት በግል መጠየቅ አይችሉም::

31.2 ማንኛውም የሥራ አመራር ኮሜቴ በተናጠልም ይሁን ወይም በወል(በጋራ) የእድሩን ገንዘብ ወይም ንብረት ከአባከነ ፤ ለግል ጥቅም ካዋለ፤ ከመመሪያ ወይም ከእድሩ ደንብ ውጪ ግለሰብን ለመጥቀም ሆነ ለመጉዳት ከተንቀሳቀሰ፤ ወይም በቸልተኝነት ገንዘብ፤ ንብረት እንዲጠፋ ካደረገ እድሩ አስፈላጊውን ህጋዊ እርምጃ ይወስድበታል።

## አንቀጽ 32: የእድሩ አመራር አባላት አገልግሎት ዘመን

32.1 የእድሩ አመራር አባላት የአገልግሎት ዘመን ሁለት ዓመት ነው። በአመራር ላይ ያለ አባል ለሁለተኛ ጊዜ ከተመረጠ ተጨማሪ ሁለት አመት በተከታታይ አራት ዓመት ሊያገለግል ይችላል:: አራት አመት ወይም ሁለት ተርም ከአገለገለ በኋላ ለሦስተኛ ጊዜ ከመመረጡ በፊት ቢያንስ አንድ ያገልግሎት ዘመን (አንድ ተርም) አርፎ በቀጣይ ምርጫ ሊመረጥ ይችላል እንጂ ለሦስት ተከታታይ የአገልግሎት ዘመን ሊመረጥ እና ሊያገለግል አይችልም::

32.2 አገልግሎት እየሰጡ ካሉት አመራር አባላት መሃል ሦስቱ ሲመረጡ በአገኙት የድምጽ ብልጫ የአገልግሎት ዘመናቸው 4 ዓመት ይሆናል:: (ሁለት ተከታታይ ተርም) የቀሪዎቹ ስድስት አመራር አባላት የሥራ ዘመን ግን 2 ዓመት ብቻ ይሆናል:: ይህ እንዲሆን ያስፈለገበት ምክንያት ሁሉም በአንዴ አስረክበው ከወጡ አዲሶቹ ተመራጮችሥራውን ባግባብ ለመምራትጊዜ ስለሚወስድባቸው ወይም ተተኪዎቹ ለሥራው አዲስ ስለሚሆኑ ተገቢውን አገልግሎት ለማበርከት በደንቡ መሠረትም ለመንቀሳቀስ ስለሚቸገሩ ሦስቱ አባላት በማለማመድ ሥራው በአግባቡ እንዲቀጥል ልምድ ያካፍላሉ ተብሎ ስለታመነበት ነው::

32.3 አዲስ ምርጫ በሚደረግበት ወቅት የሥራ ክፍፍል ወይም ምደባ ሲደረግ ቀደም ብለው ሲያገለግሉ የነበሩ እና ለሁሉት ዓመት እንዲቀጥሉ ደንብ የሚፈቅድላቸው አባላትም ከነበሩበት ሀላፊነት ተነስተው እንደ አዲስ ተመራጭ በአዲሱ የሥራ ክፍፍል ውስጥ ይመደባሉ።

## አንቀጽ 33: የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ቀን እና ቦታ

33.1 ጠቅላላ ጉባኤው በአመት አንድ ጊዜ ብቻ ይሰበሰባል። የሚሰበሰብበት ቀን፤ ቦታ እና ሰዓት በአመራር ኮሚቴው ተወስኖ ቢያንስ ቢያንስ ከ15 ቀን በፊት ጥሪ ይደረጋል::

33.2 የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ የሚያስፈልጋቸው ጊዜ የማይሰጡ አጣዳፊ ጉዳዮች ከተከሰቱ እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ወይም ልዩ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል::

33.3 ከጠቅላላ አባላት መሃል ሁለት ሦስትኛ (2/3) የሚሆኑ የእድሩ አባላት ጠቅላላ ጉባዔ እንዲጠራ በጽሁፍ በፊርማቸው አረጋግጠው ከጠየቁ አስቸኳይ የስብሰባ ጥሪ ይደረጋል::

33.4 የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ለማካሄድ እና ውሳኔ ለማስተላለፍ ከመደበኛ አባላት መሃል ከሁለት ሦስተኛው (2/3ኛ) በላይ አባላት በስብሰባው ላይ መገኘት አለባቸው:: የእድሩን ህልውና የሚመለከት ጉዳይ ከሆነ ግን ከሰባ አምስት ፐርሰንት (75%) በላይ አባላት በስብሰባው ላይ መገኘት አለባቸው።ይህ ካልሆነ የእድሩን ህልውና አስመልክቶ መወያየት ቢቻልም ውሳኔ ማሳለፍ ግን አይቻልም።

## አንቀጽ 34: የስብሰባ ሥርዓት

34.1 የእድሩ ሰብሳቢ የአባላት ምልዓተ ጉባዔው መሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ የእለቱ ስብሰባ እንዲቀጥል ያደርጋል::

34.2 የስብሰባው ምልዓተ ጉባኤ ተሟላ የሚባለው ከመደበኛ አባላት መሃል ***ሁለት ሦስትኛ (2/3 ኛው)*** አባላት በስብሰባው ቦታና ሰዓት በአካል ሲገኙ ብቻ ነው::

34.3 ምልአተ ጉባዔ መሟላቱን ሰብሳቢው ካረጋገጠ በኋላ ፤ የእለቱን መወያያ አጀንዳ በፅሑፍ ያቀርባል:: ጠቅላላ ጉባዔውም የእለቱን መወያያ አጀንዳ ካዳመጠ በኋላ ከቤቱ የሚጨመር አጀንዳ ካለ ተጨምሮ በቅደም ተከተል ጉባኤው ይወያይበታል። ምልዓተ ጉባኤው ከአልተሟላ ግን፤ ስብሰባው ለሌላ ቀን ይተላለፋል።

34.4 በሁለተኛውም የስብሰባ ቀን ማልዓተ ጉባኤው ከአልተሟላ የእድሩን ሕልውና የማይመለከት አጀንዳ እስከ ሆነ ድርስ በእለቱ በተገኘው የአባላት ቁጥር ስብሰባው ይካሄዳል ውሳኔም ይተላለፋል። የእድሩን ህልውና የሚመለከት አጀንዳ ከሆነ ግን በንኡስ አንቀጽ 33.4 መሰረት ሰባአምስት ፐርሰንት(75%) እና ከዚያ በላይ አባላት በስብሰባው ላይ መገኘት አለባቸው።ይህ ቁጥር ካልተሟላ የሚወሰነው ውሳኔ በሥራ ላይ ማዋል ፍጹም አይቻልም።

34.5 ማንኛውም ለውይይት የቀረበ ሃሳብ በአግባቡ ከተንሸራሸረ እና ከተብላላ በኋላ ሃሳቡ በድምጽ አሰጣጥ ስራአት ይወሰናል። በስብሰባ ላይ የተገኘው ማንኛውም የእድሩ አባል ሐሳቡን ያለምንም ተጽዕኖ እና ገደብ በሥርዓት ያሰማል።

## አንቀጽ 35: ውሳኔ አሰጣጥ

35.1 በእድሩ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባም ሆነ በአመራር አባላት ስብሰባ ለሚነሱ ጉዳዮች በጉባዔው አባላት መሃል ሐሳቡ በአግባቡ ከተንሸራሸረ እና ከተብላላ በኋላ ለውሳኔ ሐሳብ ሲቀርብ በዲሞክራሲያዊ አግባብ በድምጽ ይወሰናል:: የብዙሀኑን ድጋፍ /ድምፅ/ ያገኘ የውሳኔ ሐሳብ ፀድቆ ሥራ ላይ ይውላል::

35.2 ከጉባዔው የተገኘው የድጋፍ ድምጽ ከተቃውሞ ድምፅ ጋር እኩል ከሆነ ሀሳቡ እንደገና ወደ መድረኩ ተመልሶ ሰፋ ያለ ውይይት ተድርጎበት በሚገባ ከተብላላ በኋል ለሁለተኛ ጊዜ ለድምጸ ውሳኔ ይቀርባል። ለሁለተኛ ጊዜ እኩል ድምጽ ከመጣ ሰብሳቢው የሚደግፈው ሐሳብ ተቀባይነት ያገኛል::

35.3 ውሳኔው የእድሩን ሕልውና የሚመለከት ከሆነ ግን ሦስት አራተኛ (ወይንም 75%) የአባላት ድጋፍ ማግኘት አለበት። ይህ ካልሆነ ውሳኔው ተቀባይነት አያገኝም።

35.4. የድምጽ አሰጣጥ ሂደት አንድ ቤተሰብ አባል አንድ ድምጽ ነው ያለው፤ በመሆኑም ባልና ሚስት በስብሰባ ላይ ተገኝተው ሀሳብ ለመስጠት መወያየት ይችላሉ፤በድምጽ አሰጣጥ ጊዜ ግን ከሁለቱ አንዱ ብቻ ድምጽ ይሰጣል። ማለትም ባልና ሚስት በአንድ የስብሰባ ወቅት አንድ ድምጽ ብቻ ነው የሚኖራቸው።

## አንቀጽ 36: የእድሩ ማህተም አጠቃቀም፤ አቀማመጥ::

36.1 የእድሩ ማህተም ሕጋዊ /ኦፊሴላዊ/ በሆኑ ሰነዶች ላይ የሰብሳቢው ወይም የም/ ሰብሳቢው ፊርማ በአረፈበት ሰነድ /ደብዳቤ/ ላይ ማህተም መጠቀም ህጋዊ ነው:: ሰብሳቢው ወይም ም/ሰብሳቢው በማይገኙበት ወቅት አስቸኳይ ጉዳይ ካጋጠመ እና ወሳኝ ባልሆኑ፤ የፖሊሲ ጉዳዮችን በማይመለከቱ ቀላል እና ሩቲን በሆኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ በጸሐፊው ፊርማ በሰነዱ ላይ ማህተም መጠቀም ይቻላል።

36.2 ማህተሙ በእድሩ ፀሐፊ ሃላፊነት እና ጥበቃ ሥር ይቀመጣል።

36.3 አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት እንደ ህጋዊ እና ኦፊሴላዊ ሰነድ በሚቆጠሩ ሌሎች ሰነዶች ላይ ማህተም መጠቀም ይቻላል።

## አንቀፅ 37: የእድሩ አድራሻ

37.1 የመረዳጃ እድሩ የራሱ የሆነ ቋሚ ቢሮ እና አድራሻ እስኪኖረው ድረስ የእድሩ ሰብሳቢ ሆኖ የሚመረጠው አባል አድራሻ የእድሩ አድራሻ ሆኖ ያገለግላል።

37.2 እድሩ የራሱ የሆነ ፖስታ ሳጥን እና አድራሻ ይኖረዋል። የእድሩ ቋሚ አድራሻ ወይም ፅ/ቤት ሲቋቋም ፅ/ቤቱ ከፊኒክስ እና ከፊኒክስ ኩታ ገጠም እና አጎራባች ከሆኑት ከተሞች ውጭ ሊሆን አይችልም::

## አንቀጽ 38: የመረዳጃ እድሩን ደንብ ስለማሻሻል

38.1 የአንድነት መረዳጃ እድር የተቋቋመበትን ዋና ዓላማ እስካልተጣሰና፣ እስከአላፋለሰ ድረስ፤ ለእድሩ ሕልውና እና እድገት፤ ለአባላት ጥቅም እና የተሻለ አገልግሎት መስጠት እንዲያስችል ታስቦ የቀረበ ጥያቄ ከሆነ ከመደበኛ አባላት መሃል **ሁለት ሶስተኛ (2/3ኛ) እና ከዚያ በላይ ቁጥር ያላቸው** አባላት የእድሩ ደንብ እንዲሻሻል በጽሁፍ በፊርማቸው አረጋግጠው ከነምክንያቱ ለእድሩ አመራር ካቀረቡ ለጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ ከጠቅላላ ጉባኤ አባላትመሐል በ3/4ኛው አባላት (ከ75% በላይ በሆኑ አባላት) ከተደገፈ ሊሻሻልይችላል::

## አንቀጽ 39: የእድሩ ድረ ገጽ

የመረዳጃ እድሩ እንደማንኛውም ህጋዊ ተቋም የራሱ ማህበራዊ ድረገጽ አለው:: የመረዳጃ እድሩ ከሚገለገልባቸው ሶሻል ሚዲያዎች መሃል አንዱ ስለሆነ የእድሩ ድረገጽ ተዘጋጅቶ ላባላት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። የእድሩም ዌብሳይት ***azedir.com***

## አንቀጽ 40: ደንቡን ያፀደቁ መስራች አባላት ስም እና ፊርማ

አቶ ጌቱ ታዬ ---------------------------------------------

አቶ ግዛቸው ግርማይ ------------------------------------

አቶ ወንድሙ ጌታሁን --------------------------------- -

አቶ ተድላ አብርሃም ----------------------------------------

***<u>እግዚአብሔር ይህንን መረዳኛ እድርአናአባላቱን ይባርክ</u>***

***አሜን!!***